**አዋጅ ቁጥር ............/2001**

# የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ

በኢትዮጵያ ህዝቦች የዕድገት ፍላጎት መሰረት ተቋማት አስተማማኝ የማስፈፀም ዓቅም ግንባታ ዓቅሞች እንዲሆኑ የሚያበቃ ተቋማዊ ለውጥን እንዲያረጋግጡ ለማስቻል ሕጋዊ ስርዓትን መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

ተቋማት አንገብጋቢ በሆኑ የትምህርትና ምርምር አግባብነትና ጥራት ጥያቄዎች ላይ በማተኮር የኢትዮጵያ ሕዝቦች የሰላም፣ የዲሞክራሲ እና የልማት ፍላጐትን ለማሳካት አስተዋፅአዋቸውን በብቃት እንዲያበረክቱ የሚያስችል ሕጋዊ ማዕቀፍን መዘርጋት በማስፈለጉ፤

የከፍተኛ ትምህርት ሥርዓት እየተስፋፋ ባለበት ሁኔታ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን በተቋም ነፃነትና ለመንግስትና ለህዝብ ጥቅም ባጠቃላይ ባለው ተጠያቂነት መካካል ተገቢው ሚዛን እንዲጠበቅ  በሕግ መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፤

የተቋማት የአስተዳደር ስርአት በሕገ-መንግስቱ መሠረት በአመክናዊነትና ሃሳብን በነፃ የመግለፅ መርህ ላይ በተመሰረተ መመራመር የሚመራ የአካዳሚክ ማሕበረሰብን ሕይወት የሚያራምድ እንዲሆን ሕግ መደንገግ በማስፈለጉ፤

የአገሪቱ የከፍተኛ ትምህርት ባጠቃላይ በደረሰበት የእድገት ደረጃ ውጤታማ እንዲሆን ሕጋዊ አቅጣጫና አመራር በመሻቱ እና በተለይ በግል ተቋማት የሚሰጥ የከፍተኛ ትምህርት በትምህርት አግባብነትና ጥራት የሚጠበቅበትን አወንታዊ አስተዋፅኦ እንዲያበረክት የሚያስችል አቅጣጫን የሚያስይዝ ስርዓት የሚያስፈልግ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥስት አንቀፅ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር  ----------/2001" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

1/ "አካዳሚክ ማሕብረሰብ" ማለት በተቋም ውስጥ በመደበኛነት ወይም በጊዜያዊነት በመማር፣ በማስተማር እና በምርምር ተግባር ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ሰዎችን ያቀፈ ነው፤

2/ "የአካዳሚክ ሰራተኛ" ማለት በማስተማር እና/ወይም በምርምር ተግባር ላይ የተሰማራ የተቋም ሰራተኛ ሲሆን ሰኔት በሚያወጣው ደንብ መሠረት የአካዳሚክ ሠራተኛ ተብሎ እውቅና የተሰጠው ሌላ የተቋሙ ባለሙያንም ይጨምራል፤

3/ "የትምህርት ክፍል" ማለት የአንድ ተቋም አካል የሆነ ኮሌጅ፣ ፋካልቲ፣ ትምህርት ቤት፣ ኢኒስቲትዩት፣ ማዕከል ወይም ዲፓርትመንት ነው፤

4/ "የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ" ማለት የአስተዳደር፣ የቢዝነስ አመራር፣ የፋይናንስና የሂሳብ ሥራ፣ የምግብ አገልግሎት ማቅረብ፣ የጥገና፣ የጥበቃና ደህንነት ወይም የመሳሰሉትን ተግባራት የሚያከናውን የተቋም ሰራተኛ ነው፤

5/ "ኤጀንሲ" ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የሚቋቋም የትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ ነው፤

6/ "ማዕከል" ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የሚቋቋም የትምህርት ስትራተጂ ማዕከል ነው፤

7/ "ከፍተኛ ትምህርት" ማለት በስነጥበብ፣ ማሕበራዊ ሳይንስና በሳይንስና ቴክኖሎጂ መስኮች በቅድመ ምረቃና ድህረ ምረቃ የዲግሪ ፕሮግራሞች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 19 ሥር በተመለከቱት የትምህርት አግባቦች የሚሰጥ ትምህርት ነው፤

8/ "ተቋም" ማለት የመንግሥት ወይም የግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ነው፤

9/ "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የትምህርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

10/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

11/ "የግል ተቋም" ማለት በአንድ ግለሰብ ወይም ከአንድ በላይ ቁጥር ባላቸው ሰዎች ባለቤትነት ወይም ዓላማቸው ለትርፍ ባልሆነ ማሕበራት ወይም በሕብረት ስራ ማህበራት ወይም በንግድ ማሕበርነት የተመሠረተ ወይም በውጭ አገር የተመሠረተና በኢትዮጵያ ውስጥ የሚንቀሳቀስ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ነው፤

12/ "የመንግስት ተቋም" ማለት እንደ አግባብነቱ በጀቱ በፌዴራል ወይም በክልል መንግስት የሚመደብለት የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ነው፤

13/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 47 የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

14/ "የቴክኒክ ሰራተኛ" ማለት የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ ያልሆነና የመማር ማስተማርንና የምርምር ሥራን ለማገዝ የተቀጠረ ሰራተኛ ሲሆን በማስተማርያ ሆስፒታሎች ውስጥ የተቀጠረ የአካዳሚክ ሰራተኛ ያልሆነን ባለሙያንም ይጨምራል፤

15/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል::

## 3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

1/ ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚንቀሳቀስ ማንኛውም ተቋም ላይ ተፈፃሚ ይሆናል::

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ይህ አዋጅ በሃይማኖት ተቋም ሥር ባለና ዓላማውና የትምህርት ሥርዓቱ ኃይማኖት ነክ በሆነ ተቋም ላይ እንዲሁም የዲኘሎማ እና የሰርቲፊኬት ስልጠና ብቻ በሚሰጥ ተቋም ላይ ተፈፃሚ አይሆንም::

## 4. <u>የከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎች</u>

የከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፤

1/ አገሪቱ በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንድትሆን የሚያስችሏት በእውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት የታነፁ ምሩቃንን በአገሪቱ ፍላጐት መሠረት በተገቢ የሙያ መስኮችና የትምህርት ዓይነቶች ማፍራት፤

2/ በአገሪቱ ፍላጎት ላይ የተመሰረተና ትኩረቱ በቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ የሆነ ምርምርን ማራመድና ማጎልበት፤

3/ ትምህርትና ምርምር በአመክኖአዊነትና ተቀባይነት ባለው የሃሳብ ልውውጥ መርህ ላይ የተመሰረተ ሃሳብን በነፃ የመግለፅ ነፃነትን የሚያጎለብት መሆኑን ማረጋገጥ፤

4/ በአገሪቱ የዕድገት ፍላጎት ላይ የተመሰረተ የማሕበረሰብና የማማከር አገልግሎትን ማበርከት፤

5/ ተቋማዊ ነፃነትን ከተጠያቂነት ጋር ማረጋገጥ፤

6/ በተቋማት አስተዳደር የቁልፍ ባለ ድርሻዎች ተሳትፎን ማረጋገጥ፤

7/ በተቋማት እንቅስቃሴ ፍትህን፣ ፍትሃዊነትንና የሕግ የበላይነትን ማራመድና መጠበቅ፤

8/ ዴሞክራሲያዊ ባህልን ማሳደግና የማሕበረሰቡ የባህል ብዙህነትን መጠበቅ፤

9/ የመንግስት ተቋማት ስርጭት ሚዛናዊ መሆኑን ማረጋገጥና የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎን የአገሪቱ ፍላጎትንና ፍትሃዊነትን መሠረት በማድረግ ማስፋፋት::

## ክፍል ሁለት

## ስለተቋማት፣ የተቋማት ሠራተኞች እና ተማሪዎች

### ንዑስ ክፍል አንድ
### ስለተቋማት

**5. መቋቋም**

1/ በፌዴራል መንግስት በጀት የሚተዳደር ተቋም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ መሠረት ይቋቋማል::

2/ በክልል መንግስት በጀት የሚተዳደር ተቋም በክልሉ በሚወጣ ሕግ መሠረት ይቋቋማል:: ሆኖም በክልል መንግስት የሚወጣው ሕግ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችና ሌሎች የፌዴራል አነስተኛ የጥራት መመዘኛዎችን ሳይነካ መሆን ይኖርበታል::

3/ አግባብነት ያላቸው የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የግል ተቋም እንደ አግባብነቱ በማሕበራት፣ በንግድ ማሕበራት፣ በሕብረት ሥራ ማሕበራት ወይም አግባብነት ባለው ሌላ ሕግ መሠረት ይቋቋማል::

4/ ማንኛውም ተቋም የሚቋቋመው፣ የሚለወጠው ወይም ማሻሻያ የሚደረግበት የሚከተሉትን ባካተተ የፕሮጀክት እቅድ ላይ በመመሥረት ይሆናል፤

ሀ) ማሕበራዊ ተቀባይነት ያላቸው የተቋም ዓላማዎችን ያስቀመጠ፤

ለ) የተቋሙ ደረጃና ዋና ዋና አካዳሚክ ክፍሎች ዝርዝር እና የትምህርት ፕሮግራሞችና ስርዓተ ትምህርትን ያካተተ መግለጫ፤

ሐ) የተቋሙን አካዳሚክ ሰራተኞች፣ የትምህርት መገልገያዎችና የገንዘብ ምንጭን የሚገልፅ መረጃ፤

መ) ትምህርትና ምርምርን በብቃት ለማካሄድ የሚያስችል የአስተዳደር ሥርዓት ያለው ስለመሆኑ ማረጋገጫ፤

ሠ) የአገሪቱ አነስተኛ የጥራት መመዘኛዎችን የሚያከብር ስለመሆኑ የፅሑፍ ማረጋገጫ::

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ሥር የተመለከቱትን በሚመለከት ሚኒስቴሩ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል::

6/ የግል ተቋምን ለማቋቋም የሚቀርበው የፕሮጀክት ዕቅድ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ሥር ከተመለከቱት መረጃዎች በተጨማሪ ቀጥሎ የተመለከቱትን ጉዳዮች ካካተተ የመመሥረቻ ፅሁፍ ጋር መቅረብ ይኖርበታል፤

ሀ) የተቋሙን ተግባራት ወሰን፤

ለ) ተቋሙ የሚገለገልባቸውን ንብረቶችና የወጪ መሸፈኛ ምንጭ፤

ሐ) የተቋሙን የአመራር አካላትና ወኪሎች::

7/ ስለተቋም መቋቋም፣ መለወጥ ወይም መሻሻል የዚህን አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደ አግባብነቱ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚንቀሳቀስ በውጭ አገር በተቋቋመ ተቋም ወይም የተቋሙ ቅርንጫፍ ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ::

## 6. <u>ሕጋዊ ሰውነት</u>

በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመ ተቋም ሕጋዊ ሰውነት ያለው ሆኖ የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ ይችላል::

## 7. <u>የተቋማት መሪ እሴቶች</u>

ተቋማት ለተልእኳቸው መሳካት የሚያራምዱዋቸውና የሚጠብቋቸው መሪ እሴቶች የሚከተሉት ናቸው፤

1/ እውነትን የመሻትና እውነትን የመግለፅ ነፃነት፤

2/ በተልዕኮ ስኬት ላይ የተመሰረተ ታዋቂነት፤

3/ አካዳሚያዊ ተወዳዳሪነትና በትብብር ላይ የተመሰረተ ዝምድና፤

4/ የተቋም ነፃነት ከተጠያቂነት ጋር፤

5/ አሳታፊ አስተዳደርና የሕግ የበላይነት፤

6/ ፍትህና ፍትሃዊነት፤

7/ ሙስናን የመታገል ባህል፤

8/ ጥራትንና ቀልጣፋነትን ያቀናጀ አገልግሎት መስጠት፤

9/ ቆጣቢ የሃብት አጠቃቀምና ውጤታማ የንብረት ክብካቤ፤

10/ ለምስጉን ሰው እውቅና መስጠት፤

11/ ዴሞክራሲና የባህል ብዙህነት::

**8. የተቋም ሃላፊነት**

የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ተቋም የሚከተለው ሃላፊነት ይኖረዋል፤

1/ የከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎችና የተቋማት መሪ እሴቶችን የማክበር፤ የትምህርትና ምርምር ተቋም መሆኑን የማረጋገጥ፤

2/ የትምህርት ፕሮግራሞችን የመቅረፅና የከፍተኛ ትምህርትን የመስጠት፤ በአገሪቱ ፍላጐት ላይ በመመሥረት በእውቀት፣ በክህሎትና በአመለካከት የታነፁ ምሩቃንን የማፍራት እና በፕሮግራሞቹ መሠረት የተለያዩ የትምህርት ማስረጃዎችን የመስጠት፤

3/ በሃገራዊ የትኩረት አቅጣጫ መሰረት አግባብነት ያላቸው የጥናት፣ ምርምር እና የማሕበረሰብ አገልግሎትን ቅድሚያ በሚሰጣቸው ሃገራዊና ከባቢያዊ ጉዳዮች ላይ የማካሄድና ግኝቶቹንም ተገቢ በሆነ አግባብ የማሰራጨት፤ እንደ አስፈላጊነቱ ከአገር ውስጥና ከውጭ ተቋማት እና ከሌሎች የምርምር ማዕከላት ጋር በመተባበር አካዳሚያዊና የምርምር ፕሮጀክቶችን የማካሄድ፤

4/ በዚህ አዋጅና ተፈፃሚነት ባላቸው የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች መሰረት ሰራተኞቹን የመቅጠርና የማስተዳደር፤ የተቋሙን ገንዘብና ንብረትም የማስተዳደር፤

5/ በዚህ አዋጅ መሰረት የውስጥ ደንቦችና መመሪያዎችን የማውጣትና የማስፈፀም፤

6/ የተቋሙን ዕቅድ፣ በጀትና አደረጃጀት የማዘጋጀትና የመተግበር፤ እንዲሁም በዚህ አዋጅ መሠረት ያፈፃፀም ሪፖርቶችን የማቅረብ፤

7/ በተልዕኮው ላይ በመመስረት ከእንዱስትሪዎችና ሌሎች ተቋማት ጋር የትብብር ግንኙነቶችን የመመስረት፤

8/ ከፍተኛ ውጤት ላስመዘገቡ ወይም ለሕብረተሰቡ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ላበረከቱ ግለሰቦች እውቅና ወይም ሽልማት ወይም የክብር ዲግሪዎችን የመስጠት፤

9/ ለመጀመሪያና ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እገዛ ማድረግና እንደአስፈላጊነቱ ለመሰናዶና ለቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤቶች እገዛ ማድረግና ከነሱ ጋር መተባበር፤

10/ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት አመታዊና የቀደምት አመታት የትምህርት ግብአትና ውጤት እንዲሁም የፋይናንስ ገቢና ወጪ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን የማሳተም፤

11/ በዚህ አዋጅና በማቋቋሚያው ሕግ ወይም በመመስረቻው ሰነድ የተሰጠውን ሌሎች ሃላፊነቶችን የመወጣት::

**9. ስለተቋም ደረጃ**

ማንኛውም ተቋም ቀጥሎ ከተመለከቱት በአንዱ መቋቋም ይችላል፤

1/ ዩኒቨርስቲ፤

2/ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ፤

3/ ኮሌጅ፤

4/ እኒስቲትዩት::

## 10. ስለትምህርት ደረጃ

በዚህ አዋጅ ስለተቋማት ደረጃ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው በማንኛውም ተቋም የሚሰጥ ሥርዓተ ትምህርት፤

1/ በባችለር (ቢ.ኤ/ቢ.ኤስ.ሲ) ዲግሪ፤

2/ የሕክምና ዶክተር (ኤም.ዲ.) ወይም የእንስሳት ሕክምና ዶክተር (ዲ.ቪ.ኤም) ዲግሪ፤

3/ የማስትሬት ዲግሪ (ኤም.ኤ እና ኤም.ኤስሲ) ወይም የሕክምና ወይም የሌላ ሙያ ስፔሻሊቲ፤

4/ የዶክትሬት (ፒ.ኤች.ዲ) ወይም ተመሳሳይ ደረጃ ያለው ሌላ ዲግሪ፣ ወይም

5/ በሰኔት የተወሰነ ማንኛውም ሌላ ዲግሪ፣

የሚሰጥ ይሆናል::

## 11. የዩኒቨርስቲ ደረጃ ስለመስጠት

1/ ማንኛውም ተቋም "ዩኒቨርስቲ" የሚለው ስያሜና ደረጃ በሚኒስቴሩ የሚሰጠው የሚከተሉትን መመዘኛዎች ሲያሟላ ይሆናል፤

ሀ) በመደበኛ የዲግሪ ፕሮግራሙ 2,000 እና ከዚያ በላይ ተማሪዎችን ቢያንስ ከዲፓርትመንት በላይ በሆኑ ሶስት የትምህርት ክፍሎች በቅድመ ምረቃና ድሕረ ምረቃ ፕሮግራሞች የማስተማር አቅም ሲኖረው፤ ወይም በመደበኛ የዲግሪ ፕሮግራሙ 2000 እና ከዚያ በላይ ተማሪዎችን ቢያንስ ከዲፓርትመንት በላይ በሆኑ አራት የትምህርት ክፍሎች በቅድመ ምረቃ ፕሮግራም ብቻ የማስተማር ዓቅም ሲኖረው፤

ለ) በዩኒቨርስቲ ኮሌጅነት ወይም በኮሌጅነት ወይም በኢኒስቲትዩትነት የከፍተኛ ትምህርት አገልግሎት ሲሰጥ የቆየ ከሆነ በዲግሪ ፕሮግራም ቢያንስ ለአራት ተከታታይ አመታት ተማሪዎችን ያስመረቀ ሲሆን፤

ሐ) አግባብነት ባላቸው የተለያዩ መስኮች ምርምር የሚያደርግ፣ የምርምር ውጤቶቹን ያሳተመ እና የምርምር ግኝቶችን ለተጠቃሚዎች የሚያስተላልፍባቸውን መንገዶች ያመቻቸ ሲሆን፤ እና

መ) በሚኒስቴሩ የወጡ ሃገራዊ አነስተኛ የደረጃ መመዘኛዎችን የሚያሟላ ደረጃውን የጠበቀ ስርዓተ ትምህርት፣ ለስራው አስፈላጊ የሆኑ የአካዳሚክ ሰራተኞች፣ በዚህ አዋጅ የተደነገገውን ተቋማዊ የአስተዳደር አደረጃጀት፣ የማስተማሪያ ክፍሎች፣ ቤተመፃሕፍትና ቤተሙከራዎች ያለው እና ሌሎች ለየትምህርት መስኩ የሚያስፈልጉ ግብአቶችን ያሟላ ሲሆን፤

ሠ) ሌሎች በሚኒስቴሩ የተቀመጡ አነስተኛ የደረጃ መመዘኛዎችን ሲያሟላ::

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌዎች ቢኖሩም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ተቋም የዩኒቨርስቲ ስያሜና ደረጃ ይዞ እንዲቋቋም ታስቦ ከሆነና ያለው የሃብት አቅርቦትና ተቋማዊ እቅድና ራዕይ ሲታይ የታሰበው ተቋም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ሥር የተቀመጡትን መመዘኛዎች ተቀባይነት ባለው ጊዜ ውስጥ ሊያሟላ ይችላል ብሎ ሚኒስቴሩ ሲያምን ተቋሙ ዩኒቨርስቲ ሆኖ መቋቋም ይችላል::

3) በመደበኛና በርቀት ትምህርት ላይ ወይም በርቀት ትምህርት ላይ ብቻ የተመሰረተ ተቋም የዩኒቨርስቲ ደረጃን መወሰን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እንደነገሩ ሁኔታ የራሱን ጥናት በማድረግ ወይም መልካም ዓለም አቀፍ ልምድን በመጠቀም በሚኒስቴሩ የሚወሰን ይሆናል።

## 12. <u>የዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ደረጃን ስለመስጠት</u>

1/ ማንኛውም ተቋም ከሚኒስቴሩ "ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ" የሚለውን ስያሜና ደረጃ ለማግኘት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ (1) ተራ ፊደል (ሐ)፣ (መ) እና (ሠ) ከተመለከቱት በተጨማሪ፣

ሀ) በመደበኛ የዲግሪ ፕሮግራሙ ቁጥራቸው ቢያንስ 2000 የሆኑ ተማሪዎችን ከዲፓርትመንት በላይ በሆኑ ሶስት የትምህርት ክፍሎች በቅድመ ምረቃ ፕሮግራም ብቻ የማስተማር አቅም ያለው፣ እና

ለ) በኮሌጅነት ወይም በእንስቲትዩትነት የከፍተኛ ትምህርት አገልግሎት ሲሰጥ የቆየ ከሆነ በዲግሪ ፕሮግራም ቢያንስ ለሶስት ተከታታይ አመታት ተማሪዎችን ያስመረቀ፣

መሆን አለበት።

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ተቋም ያለው የሃብት አቅርቦት፣ ተቋማዊ እቅድና ራዕይ ሲታይ ተቋሙ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ሥር የተቀመጡትን መመዘኛ ዎች ተቀባይነት ባለው ጊዜ ውስጥ ሊያሟላ ይችላል ብሎ ሚኒስቴሩ ሲያምን ተቋሙ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ሆኖ መቋቋም ይችላል።

3) በመደበኛና በርቀት ትምህርት ላይ ወይም በርቀት ትምህርት ላይ ብቻ የተመሰረተ ተቋም የዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ደረጃን መወሰን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እንደነገሩ ሁኔታ የራሱን ጥናት በማድረግ ወይም መልካም ዓለም አቀፍ ልምድን በመጠቀም በሚኒስቴሩ የሚወሰን ይሆናል።

## 13. <u>የኮሌጅ ደረጃን ስለመስጠት</u>

አንድ ተቋም በሚኒስቴሩ "ኮሌጅ" የሚለውን ስያሜና ደረጃ ለማግኘት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ (1) ተራ ፊደል (መ) እና (ሠ) ከተመለከቱት መመዘኛዎች በተጨማሪ ቢያንስ ከዲፓርትመንት በላይ በሆነ አንድ የትምህርት ክፍል በዲግሪ ፕሮግራም ትምህርት የሚሰጥ መሆን ይኖርበታል።

## 14. <u>የኢኒስቲትዩት ደረጃን ስለመስጠት</u>

አንድ ተቋም ከሚኒስቴሩ "ኢኒስቲትዩት" የሚለውን ስያሜና ደረጃ ለማግኘት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ (1) ተራ ፊደል (መ) እና (ሠ) ከተቀመጡት በተጨማሪ፣

1/ ቢያንስ በአንድ የትምህርት መስክ ወይም አይነት ትምህርትና ስልጠና መስጠት የሚችል፣ እና

2/ በሚሰጠው የትምህርት አይነት በዲግሪ ደረጃ ትምህርት የመስጠት አቅም ያለው፣

መሆን ይኖርበታል፡፡

**15. አዲስ መንግሥታዊ ተቋም ስለማቋቋም**

1/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 እና 12 ድንጋጌዎች ቢኖሩም የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው አዲስ መንግስታዊ ተቋም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ በዩኒቨርስቲ ወይም በዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ደረጃ ሊቋቋም ይችላል፡፡

2/ ሚኒስቴሩ አዲሱ መንግስታዊ ተቋም ከደረጃው የሚጠበቁ መመዘኛዎችን በሙሉ ማሟላቱን ያረጋግጣል፡፡

**16. ስለአካዳሚያዊ ነፃነት**

1/ ማንኛውም ተቋም በተቋሙ ተልዕኮና በአለም አቀፍ መልካም ልምድ መሰረት አካዳሚያዊ ነፃነት ይኖረዋል፡፡

2/ ማንኛውም ተቋም የአካዳሚያዊ ነፃነቱን ሲያራምድ ማሕበረሰቡ የማሕበራዊ ሃላፊነት ባሕልን እንዲያበለፅግ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

3/ ማንኛውም ተቋም በዚህ አዋጅና በዓለም አቀፍ መልካም ልምድ መሠረት የአካዳሚያዊ ነፃነቱ አተገባበርን በስርዓት እንዲመራ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

**17. የመንግስት ተቋማት ነፃነት**

1/ ማንኛውም መንግስታዊ ተቋም ተልእኮውን ለማስፈፀም ይችል ዘንድ በዚህ አዋጅ ተቋማዊ ነፃነቱ ተረጋግጧል፡፡

2/ በዚህ አዋጅ የተደነገጉት የቦርዱና የሚኒስቴሩ ሃላፊነት እንደተጠበቁ ሆነው የመንግስት ተቋማት ነፃነት የሚከተሉትን ይጨምራል፤

ሀ) አግባብነት ያላቸውን የሥርአተ ትምህርትና የምርምር ፕሮግራሞች ማዘጋጀትና ማካሄድ፤ አዳዲስ ፕሮግራሞችን መክፈት ወይም ነባሮችን መዝጋት፤ አደረጃጀቱን መወሰንና የውስጥ ደንብንና መመሪያዎችን ማውጣትና መተግበር፤

ለ) በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የአካዳሚክና ሌሎች ሰራተኞቹን መቅጠርና ስለ ሥራ አፈፃፀም ብቃት ባስቀመጣቸው መመዘኛዎችና በሚሻው ውጤት መሰረት ኃላፊነታቸውን መወሰን፤

ሐ) በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና ተፈፃሚነት ባላቸው ሌሎች ሕጐች መርሆዎች መሰረት የሰው ሃይሉን ማስተዳደር፤

መ) በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ፕሬዚዳንቱን፣ ምክትል ፕሬዚዳንቶችን እና የቦርድ አባላትን በእጩነት ማቅረብ፤ የትምህርት ክፍሎች መሪዎችን መምረጥና መሾም፤

ሠ) በዚህ አዋጅና ተፈፃሚነት ባላቸው ሌሎች ሕጐችና ደንቦች መሠረት የገንዘብ ሃብቱንና ንብረቱን ማስተዳደር፡፡

3/ ማንኛውም የመንግስት ተቋም ነፃነቱን ሲያራምድ ሕጋዊነት፣ ቆጣቢነትና ውጤታማነት፣ ግልፅነት፣ ፍትህና ተጠያቂነትን ባረጋገጠ መልኩ መሆን ይኖርበታል፡፡

**18.** ***ስለመንግስታዊ ተቋም የአካዳሚክ ክፍሎች ነፃነት***

*1/ ማንኛውም ተቋም አሳማኝ በሆነ የትምህርት ዓይነቶች ወይም የትምህርት ዓይነት ቅርንጫፎች መጣመር ላይ የተመሰረቱ አስፈላጊ አደረጃጀት ያላቸውና ተገቢው ስያሜ የተሰጣቸው የአካዳሚክ ክፍሎች ይኖሩታል፡፡*

*2/ የማንኛውም መንግስታዊ ተቋም አካዳሚክ ክፍሎች ተቋሙ በዚህ አዋጅ መሰረት በሚያወጣቸው ድንጋጌዎች፣ መመዘኛዎችና ያፈፃፀም ስርዓት መሰረት በአስተዳደር፣ በፋይናንስና በአካዳሚክ ጉዳዮች ነፃነት ይኖራቸዋል፡፡*

*3/ የተቋማት ፕሬዚዳንቶች የአካዳሚክ ክፍሎች ባላቸው ነፃነት ሃላፊነታቸውን መወጣት እንዲችሉ አስፈላጊው ተቋማዊ ድጋፍ፣ አመቺ ሁኔታዎችና በቂ ሀብት እንዲኖሯቸው ማስቻል ይኖርባቸዋል፡፡*

**19.** ***ስለትምህርት ፕሮግራሞች***

*1/ በተለየ ሁኔታ ካልተቋቋመ በስተቀር የማንኛውም ተቋሞ ቁልፍ ተግባር በመደበኛ ፕሮግራሞች ትምህርትና ስልጠና መስጠት፣ ምርምር ማካሄድና ለማሕበረሰብ አገልግሎት መስጠት ይሆናል፡፡*

*2/ ብቃት ያለው መሆኑን ያረጋገጠ ማንኛውም ተቋም በተጨማሪ በሚከተሉት መንገዶች ትምህርትና ስልጠና መስጠት ይችላል፤*

*ሀ) ተከታታይ ትምህርት፤*

*ለ) የርቀት ወይም በመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ የሚታገዝ ትምህርት፡፡*

*3/ ብቃት ያለው መሆኑን ያረጋገጠ ማንኛውም ተቋም በተጨማሪ የማስፈፀም አቅምን ለመገንባት ወይም በአንድ የተወሰነ የሙያ መስክ እውቀትና ክህሎትን ለማስተላለፍ አጫጭር ስልጠናዎችን በመስጠት ተገቢውን ሰርቲፊኬት መስጠት ይችላል፡፡*

**20.** ***የማስተማሪያ ቋንቋ***

*1/ በሌሎች ቋንቋች ትምህርት መስጠት ወይም ጥናት ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር የማንኛውም ተቋም የማስተማሪያ ቋንቋ እንግሊዝኛ ይሆናል፡፡*

*2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም ለአጫጭር ስልጠና እና ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት መምህራን ማዘጋጃ የሚፈፀም ሙያዊ ስልጠና በተፈላጊው ቋንቋ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡*

*3/ መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች የሚሰጥ ትምህርት በምልክት ቋንቋ መሰጠት ወይም መደገፍ ይኖርበታል፡፡*

**21.** ***ሥርዓተ ትምህርት***

*1/ በማንኛውም ተቋም የስርዓተ ትምህርት ቀረፃ፣ ትግበራና የተማሪዎች ምዘና ዓላማ ተማሪው ተገቢው ሳይንሳዊ ዕውቀት፣ በነፃነት የማሰላሰል ክህሎት፣ ሃሳቡን የመግለፅ ክህሎቶችና ሙያዊ እሴቶችን እንዲጨብጥ በማስቻል ብቁ ባለሙያን ማዘጋጀት ይሆናል፡፡*

2/ ማንኛውም ተቋም የትምህርት ክፍሎቹ የስርዓተ ትምህርት ቀረፃን በተገቢ የምሩቃን ብቃት መመዘኛዎች እንዲመራ ያደርጋል፡፡

3/ ተቋማት ወቅታዊ የስርዓተ ትምህርት ቀረፃን የሚያስጠብቅ ተቋማዊ የስርዓተ ትምህርት ቀረፃ ስርዓት ይኖራቸዋል፤ የትምህርት ክፍሎቻቸው ስርዓቱን ስለመተግበራቸውም ያረጋግጣሉ፡፡

4/ ከአንድ ባላይ ብዛት ላላቸው የመንግስት ተቋማት የጋራ የሆነ ስርዓተ ትምህርት በነዚሁ ስርዓተ ትምህርቱን በሚተገብሩ የመንግስት ተቋማት ተሳትፎ በጋራ ሊቀረፅ ይችላል፤ ስርዓተ ትምህርቱም በነዚሁ ፈፃሚ ተቋማት የሚተገበር አነስተኛው መመዘኛ ሆኖ ያገለግላል፡፡

5/ ሃገራዊ ጥቅሞችና አግባብነት እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማንኛውም ተቋም በተቋማት የጋራ ተሳትፎ ስርዓተ ትምህርቶች ሊዘጋጅላቸው የሚገባ ፕሮግራሞችንም ጨምሮ ለሚሰጣቸው ፕሮግራሞች ስርዓተ ትምህርቶችን የመቅረፅና የመተግበር ነፃነት ይኖረዋል፡፡

6/ የስርዓተ ትምህርት አተገባበር በምርምርና ጥናት ላይ የተመሠረተና ወቅታዊ መሆን ይኖርበታል፤ የመማር ማስተማር ሂደቱም በዝግጅቱ፣ በአሰጣጡ እና በምዘና ስርዓቱ ሁሌም ወቅታዊ መሆን ይኖርበታል፡፡

7/ የያንዳንዱ ተቋም ስልጣን እንደተተጠበቀ ሆኖ፣ ሚኒስቴሩ ለመንግስታዊ ተቋማት የጋራ የሆኑ ስርዓተ ትምህርቶች ቀረፃን ሊያስተባብር ይችላል፤ የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎችን ለማስፈፀምም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

8/ ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሃገራዊ የሥርዓተ ትምህርት ቡድኖች ወይም ምክር ቤቶች ወይም የሥርዓተ ትምህርት ግምገማ፣ ቀረፃና ትግበራን የሚያስተባብርና የሚከታተል አካል ሊያቋቁም ይችላል፡፡

## 22. <u>ስለተቋም ጥራት ማጎልበቻ ሥርዓት</u>

1/ የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እና አግባብነት ያላቸው ደንቦችና መመሪያዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማንኛውም ተቋም አስተማማኝ የሆነና በየጊዜው የሚሻሻል የጥራት ማጐልበቻ ሥርአት ይኖረዋል፡፡

2/ የማንኛውም ተቋም ውስጣዊ የጥራት ማጎልበቻ ሥርዓት የአካዳሚክ ሰራተኞች የሙያ ልማትን፣ የትምህርት ይዘትን፣ የመማር ማስተማሩ ሂደትን፣ የተማሪዎች ምዘናና ውጤት አሰጣጥን ያካተተ ግልፅና የተሟላ የጥራት መለኪያን የያዘ መሆን ይኖርበታል፤ በተጨማሪም ተማሪዎች የትምህርት ይዘትን፣ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴን፣ የምዘና፣ የፈተናና የውጤት አሰጣጥ ሥርዓቱን የሚገመግሙበት ስርዓት ይኖረዋል፡፡

3/ የጥራት ማጎልበቻ ሥርዓቱ በተቋሙ ለመማር መረጃ ለሚጠይቁ ታሳቢ ተማሪዎች ከሚሰጥ መረጃ አንስቶ ተማሪዎች ትምህርቱንና ቆይታቸውን ሲያጠናቅቁ እስከሚሰጡት ግምገማ ድረስ ባሉት በሁሉም የትምህርት አግባብነትና ጥራትን በሚመለከት ሂደት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

4/ ማንኛውም ተቋም የጥራት ደረጃ መመዘኛዎችን ማዘጋጀት፣ በየጊዜው አካዳሚያዊ ኦዲት ማድረግና በኦዲት የተመለከቱ ድክመቶችን መከታተልና ማስተካከል እንዲሁም ግምገማውን፣ የተከናወኑ ተግባራትን እና የተገኙ ውጤቶችን የሚያሳዩ ተገቢ ሰነዶችን መያዝና ለኤጀንሲውም መላክ ይኖርበታል፡፡

5/ ተቋማት ጥራት ማጎልበትን አስመልክቶ መውሰድ ስለሚገባቸው እርምጃዎች በኤጀንሲው የሚሰጡ ተገቢነት ያላቸው አስተያየቶችን የመፈፀም ግዴታ አለባቸው፡፡

6/ የተቋም የጥራት ማጎልበቻ ሥርዓትን የሚመለከቱ ዝርዝር ጉዳዮች በተቋሙ የውስጥ ደንብና መመሪያዎች መካተት ይኖርባቸዋል፡፡

7/ ሚኒስቴሩ፣ ማዕከሉና ኤጀንሲው የተመራቂዎች ቁልፍ ባህሪያትን ወይም የምሩቃን የብቃት መመዘኛዎችን እንደየነገሩ ሁኔታ በሚወስን ወይም በሚያመላክት ሃገራዊ የምሩቃን ብቃት ማዕቀፍ አማካኝነት ጭምር የተቋማት ጥራትን የማጎልበት ጥረትን እና የሥርአተ ትምህርት ቀረፃን አቅጣጫ ያስይዛሉ፡፡

## 23. <u>ስለ አካዳሚክ ምክርና ድጋፍ</u>

1/ ማንኛውም ተቋም አግባብነት ባላቸው ክፍሎችና በአካዳሚክ ሰራተኞቹ አማካኝነት በተቋሙ ስለሚሰጡ የትምህርት አይነቶች እና ስለትምህርቱ ይዘት፣ አደረጃጀትና እና የተማሪዎች ምዘና ስርዓት በተገቢ ተቋማዊ ስርዓት ለተማሪዎቹና ለአመልካቾች መግለፅ ይኖርበታል፡፡

2/ ማንኛውም ተቋም በየትምህርት አይነቱ በትምህርት ላይ ቆይታቸው ጊዜ በሙሉ ለተማሪዎች የአካዳሚክ የምክርና የድጋፍ አገልግሎት መስጠት ይኖርበታል፡፡

3/ የአካዳሚክ ምክርና ድጋፍ አገልግሎቱ ልዩ አካዳሚያዊ ድጋፍ የሚያሻቸው ተማሪዎች መኖራቸውን ከጠቆመ የተቋማት የትምህርት ክፍሎች ድክመቶቹን ለማስወገድ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ይኖርባቸዋል፡፡

4/ ተቋማት እንዳስፈላጊነቱ የትምህርት መስኮች ምርጫን አስመልክቶ ለተማሪዎች የቅድመ ቅበላ የማማከር አገልግሎት ሥርዓትን ለመመሥረት የሚያስችላቸው እርምጃን ይወስዳሉ፡፡

## 24. <u>ምርምርና የምርምር አቅጣጫዎች</u>

1/ በማንኛውም ተቋም የሚካሄድ ምርምር በዋናነት የትምህርት አግባብነትና ጥራትን ለማሳደግ እና በቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ ባተኮሩ የአገሪቱ የልማትና ዕድገት ጉዳዮች ላይ ይሆናል፡፡

2/ ማንኛውም ተቋም ከቁልፍ የውስጥና የውጭ ባለድርሻ አካላት ጋር በመመካከር በሀገር ፍላጐት፣ በተቋሙ ተነፃፃሪ ሙያዊ ዓቅም እና ባለው የገንዘብ ሀብት የተወዳዳሪነት ብልጫው ላይ ተመሥርቶ ምርምር የሚደረግባቸው ጉዳዮች ቅደም ተከተልን መለየት ይኖርበታል፡፡

3/ ማንኛውም ተቋም የሚያካሂደው ምርምር በተለይ፣

ሀ) በአገሪቱ ቀዳሚ ፍላጎት ላይ በመመስረት በቴክኖሎጂ ሽግግር ችግር ፈቺ የሆነና የማስፈፀም ዓቅምን የሚገነባ፣

ለ) አግባብነት ያላቸው ቀጣይ ጥናቶችና ምርምሮችን ለማካሄድ እንዲችሉ ተማሪዎችን በመሠረታዊ የምርምር ዕውቀትና ክሂሎት የሚያስታጥቅ፣

መሆን አለበት፡፡

4/ ማንኛውም ተቋም በዕቅድ ላይ የተመሰረተ የራሱ ምርምርን ለማካሄድና የምርምር ፕሮጀክቶችን ከሌሎች ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ተቋማት፣ የምርምር

አካላት እና እንዱስትሪዎች በጋራ ለማካሄድ የሚያስችለው ተቋማዊ ስርዓት ይኖረዋል፡፡

5/ ምርምር ማካሄድን የሚመለከቱ የአደረጃጀትና የማኔጅመንት ዝርዝር ጉዳዮች በተቋሙ የሚወሰኑ ይሆናሉ፡፡

6/ ማንኛውም ተቋም አከራካሪ ጉዳዮችን አብራርቶ በመደንገግ እና ዓቅምና ተፈፃሚነትን ግምት ውስጥ በማስገባት በምርምር አጀንዳውና ዕቅዱ መሰረት አካዳሚክ ሠራተኞቹን በዋናነት በመምህርነት ወይም በተማራማሪነት ወይም ሁለቱንም በማቀናጀት እንዲያካሂዱ አድርጐ የሚያሰማራበት ግልጽነት ያለው ሥርዓት ይኖረዋል፡፡

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ተቋም እያንዳንዱ የአካዳሚክ ሠራተኛውን በሥነ-ጽሑፍ ላይ በተመሰረተ ጥናት ወይም በልማትና ዕድገት ጉዳዮች ላይ ባተኮረ ምርምር ላይ መሠማራቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

8/ ማንኛውም ተቋም ይህ አዋጅ ተፈጻሚ መሆን ከሚጀምርበት ቀን ጀምሮ ባሉት 300 ቀናት ውስጥ ወይም አዲስ የሚቋቋም ተቋም ሲሆን ከተቋቋመበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ውስጥ የተቋሙንና የአካዳሚክ ሰራተኞቹን አፈፃፀምን የሚቃኙ የምርምርና የምክር አገልግሎት የብቃት መመዘኛዎች፣ ሙያዊ ስነምግባር እና ሃላፊነትን የደነገጉ መመሪያዎችና ያፈፃፀም ስርዓቶች ቀርፆ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

**25. <u>የምርምርና ፈጠራ ፈንድ</u>**

1/ ማንኛውም ተቋም የምርምርና ፈጠራ ፈንድ ይኖረዋል፡፡

2/ ማንኛውም ተቋም በበጀት ምደባና ሌሎች ድጋፎች በተለይ በቴክኖሎጂ ሽግግርና ማሻሻል ላይ ላተኮረ ምርምር ቅድሚያ መስጠት ይኖርበታል፡፡

3/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማንኛውም ተቋም ቅድሚያ የሚሰጠውን የምርምር ሥራ መንግስታዊ ካልሆነ ምንጭ በሚያገኘው ገቢ ተጠቅሞ ማካሄድ ይችላል፡፡ ሆኖም ተቋሙ ከመንግሥትም ሆነ መንግሥታዊ ካልሆነ ምንጭ በተለይ ለምርምር የተመደበለት ገንዘብ ቆጣቢና ውጤታማ በሆነ አግባብ ለምርምር ተግባር መዋሉን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

4/ ማንኛውም ተቋም ግልፅነት ያለው የምርምር ፈንድ አስተዳደር ሥርዓት ይኖረዋል፡፡

5/ ማንኛውም ተቋም ወይም የተቋሙ አካዳሚክ ሠራተኛ ከሌሎች አካላትና ከውጭ አገር ምንጭ በሚገኝ ገንዘብ የጋራ የምርምር ሥራ ማካሄድ የሚችለው የምርምሩ ሥራ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ (8) ሥር በተገለጸው መሰረት በተቋሙ የሥነ-ምግባር ስርዓት ክልል የሚከናወን ከሆነ ነው፡፡

**26. <u>የምክር አገልግሎት እና ሌሎች ተጓዳኝ ተግባራት</u>**

1/ ተቋማት በብቃታቸው መሠረት የምክር አገልግሎትና ተጓዳኝ ተግባራትን ሊያከናውኑ ይችላሉ፡፡

2/ የመንግስት ተቋማት የአካዳሚክ ሠራተኞቻቸው የሚካሂዱት የምክር አገልግሎትና ሌሎች ተጓዳኝ ተግባራትን ተቋሙ እንዲያከናውን የተቋቋመባቸው ሥራዎች ጥራትና አፈፃፀምን ሳይነኩ መከናወናቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

3/ የመንግስት ተቋማት በአካዳሚክም ሆነ በሌሎች ሠራተኞቻቸው የሚከናወኑ ተጓዳኝ ተግባራት ተልዕኳቸውን እና የተመሰረቱባቸው ሕጋዊና የስነምግባር መርሆዎችን የማይሸረሽሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

4/ ማንኛውም የመንግስት ተቋም ይህ አዋጅ ተፈጻሚ መሆን ከሚጀምርበት ቀን አንስቶ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወይም ተቋሙ አዲስ የተቋቋመ ሲሆን ከተቋቋመበት ቀን ጀምሮ በሁለት ዓመታት ጊዜ ውስጥ በሠራተኞቹ የሚከናወኑት የምክር አገልግሎቶች ወይም ሌሎች ተጓዳኝ ተግባራት የሚመሩበትን መመሪያ ማውጣት ይኖርበታል፡፡

5/ ማንኛውም ተቋም ከኢንዱስትሪዎች ጋር ግልፅነት ባለው ድርድርና ስምምነት መሠረት መርህን የጠበቀና የጋራ ጥቅምን የሚያራምድ ግንኙነት የመመስረት ሃላፊነት አለበት፡፡

6/ የግለሰቦች አእምሮአዊ ንብረት ባለቤትነት መብቶችና ውል የተገባበት ሚስጥርን የመጠበቅ ግዴታ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማንኛውም ተቋም ለአካዳሚክ አገልግሎት ብቻ እንዲውሉ ይደረጉ የነበሩትን ዕውቀትና ክህሎት ለሕብረተሰቡ ግልጋሎት እንዲውሉ የማድረግ ሃላፊነት አለበት፡፡

7/ ተቋማት በምክር አገልግሎቶች አማካይነት የሚያገኟቸውን ውጤቶች ለአካዳሚክ አገልግሎቱ ማዳበሪያና ለመማር ማስተመሩ ሂደት ማበልጸጊያ አንድ ምንጭ አድርገው መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡

8/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተመለከተውን ደንብ ተላልፎ በመገኘቱ አግባብነት ባለው ሃላፊ የመጀመሪያ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት በድጋሜ የመተላለፍ ሁኔታ የፈፀመ ሰው በተቋሙ የዲስፕሊን ደንብ መሠረት እርምጃ እንዲወሰድበት ይደረጋል፡፡

9/ ማንኛውም የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ ጥሰት መኖሩን የተገነዘበ የቅርብ ሃላፊ ወይም የተቋሙ ባለሥልጣን በሕጋዊ ሥርዓት መሠረት ጥሰቱን የማስቆም ሃላፊነት ይኖርበታል፤ ይህን ሃላፊነቱን ካልተወጣ ወይም ችላ ካለ የዲስፕሊን እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

## 27. <u>መረጃ ስለማግኘት</u>

1/ ተቋማት ስታቲስቲካዊ መረጃ የሚሰበሰቡበትንና በመካከላቸው፣ በክፍሎቻቸው መካከልና ከሚኒስቴሩ ጋር መረጃዎችን የሚለዋወጡበት ቀልጣፋ ሥርአት መፍጠር ይኖርባቸዋል፡፡

2/ ተቋማት ትክክለኛ፣ ዝርዝርና የተሟላ አመታዊ የትምህርትና የገንዘብ ገቢና ወጪ ስታቲስቲካዊ መረጃ ማሳተም ይኖርባቸዋል፡፡ መረጃን የማሳተሙ ግዴታ ከአቅም በላይ የሆነ ክስተት ካላጋጠመ በስተቀር አንድ የትምህርት ዘመን እንደተጠናቀቀ በአንድ መቶ ሃያ ቀናት ጊዜ ውስጥ መፈፀም ይኖርበታል፡፡

3/ በሕግ የተደነገጉ ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ምርምር ለሚያካሂዱ የአካዳሚክ ሰራተኞችና ተማሪዎች መረጃ የመስጠትና የመተባበር ሃላፊነት አለባቸው፡፡

## 28. <u>የአካዳሚክ ዘመን እና የበጀት ዓመት</u>

1/ የማንኛውም ተቋም የመደበኛ ፕሮግራም አንድ የትምህርት ዘመን እኩል በሆኑ ወሰነ ትምህርቶች የተከፈሉ 300 ቀናት ይኖሩታል፡፡

2/ የማንኛውም ተቋም ሴኔት የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ መሠረት በማድረግ የትምህርት ዘመንን ይወስናል፡፡

3/ የመንግሥት ተቋማት የበጀት ዓመት የመንግሥት በጀት ዓመት ይሆናል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## የተቋማት ሠራተኞች

**29. የሠራተኞች ዓይነት**

ማንኛውም ተቋም፣

1/ አካዳሚክ ሠራተኞች፣

2/ የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች፣

3/ የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች፣

4/ እንደ አግባቡ በማስተማሪያ ሆስፒታሎች የሚሰሩ ባለሙያዎች፣

ይኖሩታል፡፡

**30. አካዳሚክ ሠራተኞች**

1/ ማንኛውም ተቋም የሚከተሉት አካዳሚክ ሠራተኞች ሊኖሩት ይችላል፤

ሀ) ለማስተማርና/ወይም ለምርምር የተቀጠሩ ፕሮፌሰሮች፣ ተባባሪ ፕሮፌሰሮች፣ ረዳት ፕሮፌሰሮች፣ ሌክቸረሮች፣ ረዳት ሌክቸረሮች እና በሁኔታዎች አስገዳጅነትና ለመሸጋገሪያ ጊዜ የሚቀጠሩ ረዳት ምሩቆች፤

ለ) በዓለም ዓቀፍ መልካም ተሞክሮዎችና በተቋሙ ሴኔት ውሳኔና ደንብ መሠረት የአካዳሚክ ሠራተኝነት እውቅና የተሰጣቸው ሌሎች ሠራተኞች፡፡

2/ ማንኛውም ተቋም ለአካዳሚክ ሰራተኞች የማዕረግ ዕድገት የሚሰጥበትና አዲስ ቅጥርን የሚፈፅምበት ዓለም አቀፋዊ መልካም ተሞክሮ ላይ የተመሰረተ የዕድገትና የቅጥር አፈፃፀም መመሪያ ይኖረዋል፡፡

3/ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (2) የተደነገገው ቢኖርም የባችለር ዲግሪ ምሩቃን በመደበኛ አካዳሚክ ሠራተኛነት በመንግስታዊ ተቋም ሊቀጠሩ የሚችሉትና ማዕረጋቸው የሚወሰነው ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይሆናል፡፡

4/ ማንኛውም ተቋም በጥራትና በቁጥር በቂ የአካዳሚክ ሠራተኞች እንዳሉት ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ የአካዳሚክ ሰራተኞች ብዛት በተቋሙ የሚወሰን ሆኖ በተማሪ መምህር ምጣኔና ለምርምር በሚያስፈልግ ተጨማሪ ቁጥር ላይ የተመሰረተ ይሆናል፡፡

5/ በሁሉም የመንግሥት ተቋማት ውስጥ ተፈፃሚ የሚሆኑ አገራዊ የማስተማርና የምርምር ሥራዎች ጫና መስፈርት ይኖራል፡፡ መስፈርቱ በመንግሥት ተቋማት የጋራ መድረክ ተዘጋጅቶና በቦርዱ ተደግፎ በሚኒስቴሩ ሲፀድቅ ተግባራዊ ይሆናል፡፡ ሚኒስቴሩ መስፈርቱን በግል ተቋማትም ተፈፃሚ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል፡፡

6/ ሚኒስቴሩ ማንኛውም ተቋም ማሟላት ያለበትን በትምህርት ደረጃና በማዕረግ አነስተኛው የአካዳሚክ ሰራተኞች ምጣኔን በየጊዜው ያወጣል፡፡

7/ በድህረምረቃ ፕሮግራሞች ዓቅሙ በተሻለ ዕድገት ላይ የሚገኝ መንግሥታዊ ተቋም እንደ አንድ ሀገራዊ ቀዳሚ ተግባሩ ያነሰ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሌሎች መንግሥታዊ ተቋማት በአካዳሚክ ሠራተኞቻቸው ልማት ያለ ትምህርት ክፊያ እገዛ ያደርጋል፡፡

8/ አግባብነት ያላቸው የሌሎች ሕጐች ተፈፃሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ለአንድ አካዳሚክ ቅጥር ቦታ የሚያመለክት ሰው ሊቀጠር የሚችለው ከቅርብ ጊዜ አሰሪው የሥራ መልቀቂያ ማስረጃ ማቅረብ ሲችል ብቻ ይሆናል፡፡

9/ አግባብነት ያላቸው የሌሎች ሕጐች ተፈፃሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከአንድ ተቋም በዲስፕሊን ጥፋት ምክንያት የተባረረ አካዳሚክ ሠራተኛ በሌላ ተቋም መቀጠር የሚችለው የቀድሞ ታሪኩ፣ የተባረረበት ጥፋትና ከተባረረ በኋላ ያለበት ሁኔታ ታይቶና ተገምግሞ በተቋሙ ሴኔት አስቀድሞ ሲፈቀድ ብቻ ይሆናል፡፡

10/ ማንኛውም ተቋም እንደአግባብነቱ የዚህን አንቀጽ ድንጋጌዎች ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## 31. የአካዳሚክ ሠራተኛ መብት

1/ የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማንኛውም የአካዳሚክ ሠራተኛ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፤

ሀ) በተቋሙ ተልዕኮ መሰረት የአካዳሚክ ነፃነትን የመጠቀም፤

ለ) በተቋሙ የውስጥ ደንብና መመሪያዎች መሠረት ምርምር የማካሄድና ሙያዊ የምክር አገልግሎት የመስጠት፤ እንዲሁም በተቋሙ ደንብና መመሪያዎች መሠረት የሳባቲካልና የምርምር ዕረፍቶችን በመውሰድ ለተቋሙና ለሀገር ጠቃሚ የሆነ ምርምሮችና ጥናቶች የማካሄድ፤

ሐ) በተቋሙ ደንብና መመሪያ መሠረት ሙያውን የሚያዳብር ትምህርትና ሥልጠናን የማግኘት፤

መ) በተቋሙ ደንብና መመሪያ እንዲሁም እንደአስፈላጊቱ በሚኒስቴሩ በሚወጣ ሀገራዊ መስፈርት መሠረት የሙያ ዕድገትን የማግኘት፤

ሠ) ግልፅና ፍትሃዊ አስተዳደር የማግኘትና የሀገሪቱ የኢኮኖሚ አቅም በሚፈቅደው መሠረት በመንግስት የሚወሰን ወይም በግል ተቋሙ ዓቅም ላይ የተመሠረተ ደሞዝና ጥቅማጥቅሞችን የማግኘት፤

ረ) በተቋሙ የትኩረት አቅጣጫ፣ ዕቅድና የደንብና መመሪያዎች ዝግጅትና የስርዓተ ትምህርት ቀረፃ ላይ እንደአመቺነቱ የመሳተፍና በመማር ማስተማር ሂደት አግባብነትና ጥራት ላይ አስተያየት የማቅረብ፤

ሰ) ስለ ስራ አፈፃፀሙ የተደረገ ግምገማ ውጤትንና ያለእርሱ ዕውቀት በግል ማህደሩ ውስጥ ስለተቀመጡ መረጃዎች የማወቅ፤ እንዲሁም በማህደሩ ውስጥ የሚቀመጡ መረጃዎች ለተቋሙ አስተዳደራዊ ጉዳይ ወይም አግባብ ባለው ሕግ በተደነገገው መሠረት ካልሆነ በስተቀር በሚስጢር እንዲያዙለት የማድረግ፤

ሸ) በተቋሙ ግቢ ውስጥ የራሱና የግል ንብረቱ ደህንነት ተጠብቆ ተገቢውን አገልግሎት የመስጠት፤

ቀ) ስለተቋሙ ዕቅድ፣ ዕድገት፣ የትኩረት አቅጣጫ፣ ሁኔታና የክንውን ውጤቶች መረጃ የማግኘት፤

በ) አካዳሚክ ሠራተኛን መምረጥ ተገቢ በሆነበት ሁሉ የመመረጥና የመምረጥ፤

ተ) በዲስፕሊን ጉዳይ የመሰማት እድል የማግኘትና ተገቢ ያልሆነ ውሳኔ እንዲነሳለት የመጠየቅና ፍትህን የማግኘት።

2/ ማንኛውም ተቋም አካዳሚክ ሠራተኞቹን በሚመለከቱ የሙብት ጉዳዮች ላይ በአሳታፊ ሂደት መመሪያና ያፈፃፀም ስርዓትን የመቅረፅና ተግባራዊ የማድረግ ሃላፊነት አለበት።

## 32. የአካዳሚክ ሠራተኛ ግዴታ

1/ ማንኛውም የተቋም አካዳሚክ ሠራተኛ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፤

ሀ) ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ልዩ ድጋፍ ማድረግን ጨምሮ የማስተማር፣ የአካዳሚክ ምክር አገልግሎትና የሕብረተሰብ አገልግሎት የመስጠት፤

ለ) በራሱ የሙያ መስክና ብቃት መሰረት ለሀገር ጠቃሚ የሆነ ችግር ፈቺ ጥናትንና ምርምርን የማካሄድና ቴክኖሎጂን የማሸጋገር፣ ወይም ቢያንስ የሚያስተምረውን ትምህርት በጥናትና ምርምር ላይ የተመሰረተ የማድረግና በየጊዜው የማሻሻል፤

ሐ) ሥርዓተ ትምህርትን በመገምገም፣ በመቅረፅና በማጎልበት ሂደት ላይ የመሳተፍና ተገቢውን ሚና የመጫወት፤ እንዲሁም በሥርዓተ ትምህርቱ አተገባበር፣ በተማሪዎች ምዘና፣ ውጤት አሠጣጥና ማማከር፣ የተማሪዎችን ቅሬታዎችና አቤቱታዎችን በማስተናገድ እና ባጠቃላይ በሙያዊ ሥነ-ምግባር የሚጠበቅበትን ሙያዊ ብቃት የማረጋገጥ፤

መ) የከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎችንና ተቋሙ የሚመራባቸውን እሴቶች የማክበር፣ የመተግበርና አካዳሚክ ነፃነቱን በሙያዊ ስነምግባር እና አግባብነት ባላቸው የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የመጠቀም፤

ሠ) ተማሪዎች የተቋሙን ተልዕኮ፣ መሪ እሴቶችና የከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎችን እንዲያውቁ የመምከር፣ የማገዝና የመርዳት፤

ረ) ሙሉ የሥራ ጊዜውን ለተቋሙ የማዋል፤

ሰ) በመማር-ማስተማር ሂደት የራስን ፖለቲካዊ አመለካከት ወይም ሃይማኖት በተማሪዎ ቹ አመለካከት ላይ ከመጫን የመቆጠብ፤

ሸ) ከተቋሙ ማሕበረሰብ አባላት በሚኖረው ግንኙት በሕገ መንግሥቱ የተረጋገጡ መብቶችን ከሚፃረሩ ድርጊቶችና አሰራሮች የመቆጠብ፤

ቀ) በተቋሙ የማቋቋሚያ ሕግ ወይም መመሥረቻ ሰነድ እና በተቋሙ የሰኔት ደንብ መሠረት የሚሰጡት ሌሎች ተግባራትን የማከናወን።

2/ አካዳሚክ ሰራተኞች የሆኑ የጤና ባለሙያዎች በተቋሙ የማስተማሪያ ሆስፒታል ውስጥ በሙያቸው ተገቢውን አገልግሎት የመስጠት ግዴታም ይኖርባቸዋል።

3/ ተቋማት በዚህ አንቀጽና አግባብነት ባላቸው የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች ላይ የተመሰረተና የአካዳሚክ ሠራተኞችን ያሳተፈ የአካዳሚክ ሠራተኞች የዲስፕሊን መመሪያ አውጥተው ተግባራዊ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

4/ ማንኛውም ተቋም በዚህ አንቀጽ ንዑስ (3) የተመለከተውን መመሪያ ይህ አዋጅ ተፈጻሚ መሆን ከሚጀምርበት ወይም አዲስ ተቋም ሲሆን ከተቋቋመበት ቀን አንስቶ ባሉት 300 ቀናት ውስጥ በማውጣት ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## 33. ስለአካዳሚክ ሠራተኞች ቋሚነትና የጡረታ መውጫ ዕድሜን ስለማራዘም

1/ እንደ ልዩ ጥቅምና ለሙያ ልቀት ማበረታቻ እንዲሆን አንድ አካዳሚክ ሠራተኛ ቋሚ ቅጥር ሊደረግ ይችላል፤ የአካዳሚክ ሰራተኛ ቋሚ ቅጥር የሚሆነው በሰጠው አገልግሎትና ባበረክተው የማስተማር እና/ወይም የምርምር ምሁራዊ አስተዋጽኦ ወይም ባስመዘገበው የተቋም መሪነት ብቃት ላይ ተመሥርቶ ይሆናል፡፡

2/ ቋሚ የሆነ የአካዳሚክ ሠራተኛ የሥራ ዋስትና ይኖረዋል፤ ቋሚ የሆነ የአካዳሚክ ሠራተኛ ከሥራው ሊባረር የሚችለው በመንግስት ተቋሙ የሰኔት ደንብ መሠረት ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ፈጽሞ ሲገኝ ብቻ ይሆናል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን የሚያሟላ ኘሮፌሰር ወይም ተባባሪ ኘሮፌሰር በጡረታ ከተገለለ በኂላም ማዕረጉን እንደያዘ እንዲቀጥል በተቋሙ የሰኔት ደንብ መሠረት ሊፈቀድለት ይችላል፡፡

4/ ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ሁኔታዎች ከተሟሉ በመንግሥታዊ ተቋም የሚያገለግል አካዳሚክ ሠራተኛ የጡረታ መውጫ ዕድሜን ለእያንዳንዱ ጊዜ በሶስት ዓመት የሚታሰብ ሆኖ ለሁለት ጊዜያት እንዲራዘም ሊያደርግ ይችላል፤

ሀ) የአካዳሚክ ሠራተኛው የማስትሬት ዲግሪ ወይም ከዚያ በላይ ኖሮት መልካም ጤንነት ያለውና ተከታታይና ውጤታማ አገልግሎት ሲሰጥ የቆየ ከሆነ፣

ለ) ተቋሙ በወቅቱና በወደፊት ፍላጎቱ ላይ ተመሥርቶ የጡረታ ዕድሜው መራዘሙ ተገቢ መሆኑን ማስረዳት ከቻለ፣

ሐ) የአካዳሚክ ሠራተኛው የጡረታ መውጫ ዕድሜው እንዲራዘምለት ፈቃደኛ ከሆነ፡፡

5/ ሚኒስቴሩ የዚህን አንቀጽ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ለማድረግ መመሪያ ያወጣል፡፡

## 34. አካዳሚክ ሠራተኛን በጋራ ስለመቅጠር

1/ አካዳሚክ ሠራተኛን በጋራ መቅጠር ተፈጻሚ የሚሆነው የትምህርት አግባብነትና ጥራትን ለማረጋገጥ መልካም መፊትሄ ሆኖ ሲገኝ ወይም የአካዳሚክ ሠራተኛ እጥረትን ለመቅረፍ አስፈላጊ ሲሆን ነው፡፡ የጋራ ቅጥር ተግባራዊ ሲደረግ የማስተሬት ዲግሪ እና ከዚያ በላይ የትምህርት ደረጃ ያለውን የአካዳሚክ ሠራተኛን የሚመለከት ሆኖ ከኢንዱስትሪ፣ ከንግድ፣ ከምርምር ማዕከሎች ወይም ከሌሎች ድርጅቶች በጋራ ቅጥር በተቋም ለመሰማራት የሚያበቃ ሙያዊ ዓቅም ያለው ባለሙያንም የሚመለከት ይሆናል፡፡

2/ የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎችና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጐች ተፈጻሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አንድ አካዳሚክ ሠራተኛ ወይም የመንግሥት ሰራተኛ ዓቅሙ ካለው በራሱ ፈቃድና በተቋሙ ወይም በመሥሪያ ቤቱ ፈቃድ በጋራ ቅጥር

ሊሰማራ ይችላል:: የሰው ሃይል እጥረት ባለባቸው አንዳንድ መስኮች፣ ተቋማትና መሥሪያ ቤቶች ወይም ድርጅቶች አካዳሚክ ሠራተኞችን ወይም የመንግሥት ሠራተኞችን በጋራ ለመቅጠር የመተባበር ግዴታ አለባቸው::

3/ የቅጥሩ ሁኔታ፣ ቅጥሩ የሚቆይበት ጊዜ፣ ደመወዝና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች፣ እንዲከናወኑ የሚፈለጉ ተግባራትና ጊዜን ማደላደል የመሳሰሉት ለተቀጣሪውና ለአሠሪዎቹ ወሳኝ የሆኑ ጉዳዮች የሚመለከተው ሰኔት በሚያወጣው መመሪያና ሥርዓት መሠረት በስምምነት ይወሰናሉ::

4/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች የመንግስት ተቋም አካዳሚክ ሠራተኛ ወይም ሌላ የመንግስት ሰራተኛ በግል ተቋም የጋራ ተቀጣሪ ሆኖ የመቀጠር መብት እንደሰጡ ተደርገው ሊወሰዱ አይችሉም::

5/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሚኒስቴሩ ተቋማት የራሳቸውን ዝርዝር መመሪያና የሥነ ሥርዓት ደንብ እንዲያወጡ የሚረዳ መመሪያን ይህ አዋጅ ተፈጻሚ መሆን ከሚጀምርበት ቀን አንስቶ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ያወጣል::

## 35. <u>የአስተዳደርና የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች</u>

1/ የመንግሥት ተቋማት የቴክኒክና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 36 ንኡሰ አንቀፅ (3) እና አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ (1) ተራ ፊደል (በ) መሠረት ቦርድ በሚያወጣው ፖሊሲና መመሪያ መሠረት ይተዳደራሉ::

2/ አካዳሚክ ባለሙያዎች ያልሆኑና በማስተማሪያ ሆስፒታሎች የተቀጠሩ የቴክኒክ ሠራተኞች የሚተዳደሩት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በሚወጡት ፖሊሲዎችና መመሪያዎች ይሆናል፤ ሆኖም የደመወዝ ክፍያቸው በመንግስት የጤና ጥበቃ ዘርፍ ለተመሳሳይ ባለሙያዎች ተፈጻሚ በሚሆነው መሠረት ይሆናል::

3/ መንግሥታዊ ተቋማት የአስተዳደርና የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞቻቸው ተፈላጊውን የብቃት ደረጃ ያላቸው መሆናቸውንና ቁጥራቸውም ከተፈላጊው ቁጥር ያልበለጠ መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ ይኖርባቸዋል::

4/ መንግሥት በጀት ሲመድብ የመንግሥት ተቋማት ተፈላጊውን የአስተዳደና የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ቁጥር ብቻ እንዲኖራቸው የሚያስችላቸውን መጠን መመደቡን ያረጋግጣል::

5/ ማዕከሉ ከመንግስታዊ ተቋማት ጋር በመሆን የሚያስፈልገውን የቴክኒክና የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ትክክለኛ ቁጥር ለመወሰን የሚረዳ የምጣኔ መስፈርትን ይህ አዋጅ ተፈፃሚ መሆን ከጀመረበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ያወጣል::

6/ የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) ድንጋጌዎችን ተፈጻሚነት እንዲያግዝ ማንኛውም የመንግሥት ተቋም ተገቢ አደረጃጀትና ጥንቃቄ የተሞላው የአስተዳደርና የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ቅጥር አፈጻጸም እንዲኖረው የማድረግ ግዴታ አለበት::

7/ የመንግስት ተቋማት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) የተመለከተው የምጣኔ መስፈርት ከወጣበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞቻቸው ምጣኔን ማስተካከል አለባቸው::

**36. የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች መብትና ግዴታ**

1/ የመንግስት ተቋማት ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች አግባብ ባለው የሲቪል ሰርቪስ ሕግ መርሆዎች መሠረት መልካም አስተዳደርን የማግኘት መብት ይኖራቸዋል::

2/ ማንኛውም የመንግስት ተቋም ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን የሚመለከቱ ጉዳዮችን አስመልክቶ የአስተዳደር መመሪያን ከማውጣትና ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት በአሳታፊ ሂደት ግንዛቤና መግባባት እንዲፈጠር የማድረግ ግዴታ አለበት::

3/ የመንግሥት ተቋም ቦርድ አግባብ ባለው የሲቪል ሰርቪስ ሕግ መርሆዎች ላይ በመመስረት የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች አሰተዳደር ዝርዝር መመሪያን ማውጣት ይችላል::

4/ ማንኛውም የተቋም ድጋፍ ሰጪ ሠራተኛ አግባብነት ላላቸው ሕጎችና የተቋሙ መመሪያዎች የመገዛትና በተግባርም የከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎችንና እንደአግባብነቱ የተቋሙን መሪ እሴቶች የማክበር ግዴታ አለበት::

## ንዑስ ክፍል ሦስት

## ስለተቋማት ተማሪዎች

**37. የተማሪዎች መብት**

1/ የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎችና አግባብነት ያላቸው ሌሎች ሕጐች እንደተጠቁ ሆነው የማንኛውም ተቋም ተማሪዎች የሚከተሉት መብቶች ይኖሯቸዋል፤

ሀ) በመማርና በምርምር በነፃነት እውነትን የመሻትና ሐሳብን በነፃነት የመግለጽ፤

ለ) በመማሪያ ክፍል፣ በተቋም ግቢና በሕበረተሰብ ውስጥ ባጠቃላይ ለመማር አመቺ ሁኔታን የማግኘትና የመጠቀም፤

ሐ) በተቋም ግቢ ውስጥ ሕገ-መንግስታዊ ሰብአዊ መብታቸውንና ደህንነታቸውን ተጠብቆ የመኖርና የግል ንብረታቸውን ደህንነት የማስጠበቅ፤

መ) በተቋም ጉዳዮች ላይ በሕጋዊና ሰላማዊ አግባብ አቋማቸውን በነፃነት የማራመድ፤

ሠ) ማንኛውም ዓይነት አድልዎ ወይም ትንኮሳ እንዳይደርስባቸው ተቋማዊ ሕጋዊ ከለላን የማግኘት፤

ረ) በማንኛውም የመምህርና ተማሪ ግንኙነት ገጽታዎች የፍትህና ፍትሃዊነት ተጠቃሚ የመሆንና ለመማር የሚያበረታታ መልካም ተቋማዊ ድባብን የማግኘት፤

ሰ) ስለ አካዳሚያዊ ብቃታቸው በዚህ አዋጅ በተደነገጉ መርሆዎችና በተቋሙ አከዳሚክ መመዘኛዎች መሰረት የመመዘን፤ ኢፍትሃዊ ምዘና ሲፈፀም ቅሬታን በተቋሙ ስርዓት መሰረት በሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ የማቅረብና ፍትህን የማግኘት፤

ሸ) ግልፅነት ባለው ስርዓት መሠረት በአከዳሚክ ሰራተኞች የስራ አፈፃፀምና በአካዳሚክ ፕሮግራሞች አፈፃፀም ግምገማ ላይ የመሳተፍ፤

ቀ) በግል የትምህርት ማሕደር በቋሚነት የሚቀመጡ መረጃዎች በምስጢር ስለሚጠበቁበትና ለሌላ ወገን ስለሚገለፁበት ሁኔታ የሚወስን የሚያስተማምን ስርዓት ተጠቃሚ የመሆን፤

በ) የተማሪው የጋራ ጥቅሞችን በሕጋዊ መንገድ እንዲጠበቁ ለማስቻል አግባብነት ባላቸው ሕጐች በተቋቋመና የተቋሙን ተማሪዎች በአባልነት በሚያቅፍ የተቋሙ የተማሪዎች ማሕበር አባል የመሆን፤

ተ) በተቋሙ ደንብና ስርዓት መሠረት በማሕበራቸው አማካይነት በተቋሙ መገልገያዎች የመጠቀም፤

ቸ) በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች፣ በተቋሙ ማቋሚያ ሕግ ድንጋጌዎችና የተቋሙ ቦርድ በሚያወጣቸው መመሪያዎች መሠረት በማሕበራቸው ወይም በተወካዮቻቸው አማካይነት ተቋሙን በሚያስተዳድሩት አካላት ስብሰባዎች ላይ የመሳተፍ፤

ኀ) የሚያስከትሏቸው ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው በማሕበራቸው አመራር ስር ዜና፣ አስተያየትና ርእሰ አንቀፆችን ጨምሮ ሃሳብን በነፃ ለማንሸራሸር በተቋም ውስጥ የመገናኛ ሚዲያን የመጠቀም፤

ነ) በዚህ አዋጅ መሰረት የወጪ መጋራት ስርዓት ተጠቃሚ የመሆንና የምክር አገልግሎትን የማግኘት::

2/ ማንኛውም ተቋም በዚህ አንቀጽ የተመለከተውን የተማሪዎች መብት ማስከበሪያ የሚሆን መመሪያን የመቅረፅና የመተግበር ግዴታ አለበት፤ መመሪያው በዚህ አዋጅ መሠረት የተቀረፀና የአካዳሚክ ማሕበረሰቡን ባሳተፈ ሂደት መግባባት የተደረሰበት መሆን ይኖርበታል::

## 38. <u>የተቋም ተማሪዎች ግዴታ</u>

1/ የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎችና አግባብነት ያላቸው ሌሎች ሕጐች ተፈፃሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የተቋም ተማሪ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፤

ሀ) በክፍል የመገኘትና ትምህርቱን በሚገባ የመከታተል፤ የማንኛውም አካዳሚክ ሰራተኛ የመማር ማስተማር ሂደቱን የመምራትና የመቆጣጠር ሥልጣንን የማክበር፤

ለ) በተመዘገበበት ትምህርት የተቀመጡ የብቃት መመዘኛዎችን የማሟላት፤

ሐ) የከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎችንና የተቋሙን መሪ እሴቶች የማወቅና የማራመድ፤

መ) በክፍል ውስጥም ሆነ በተቋሙ ግቢ ውስጥ በሕግ የተጠበቀውን የሌሎች ሰዎችን መብት የማክበር፤

ሠ) አግባብነት ያላቸው የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችን እንደዚሁም በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ላይ የተመሰረቱትን የተቋም መመሪያዎችና ደንቦችን የማክበር፤

ረ) ከተቋሙ አካዳሚክና ሌሎች ሠራተኞች እንዲሁም ከማንኛውም የተቋሙ ተማሪ ጋር በሚኖረው ግንኙነት ሕገ-መንግሥታዊ መብቶቻቸውን የማክበር፤

ሰ) ከማንኛውም ሕገወጥ ድርጊት እና ከማንኛውም ከሥነምግባር ውጭ ከሆኑ ተግባራት የመቆጠብ፤

ሸ) የግልም ሆነ የጋራ የተማሪ ጥቅሞች አደጋ ላይ በሚወድቁበት ጊዜ በሠላማዊና ሕጋዊ መንገድ ቅሬታን በማሰማት መፍትሔን የመሻት፤

ቀ) የተቋሙን ንብረት በጥንቃቄ የመያዝና የመጠቀም፤ ሆነ ተብሎ ወይም በቸልተኝነት ምክንያት በተቋሙ ንብረት ላይ ለሚደርስ ጉዳት ተጠያቂ የመሆን፤

በ) በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ተቋሙ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች መከፈል የሚገባውን ክፍያ የመፈፀም፤

2/ ማንኛውም ተቋም የተማሪዎችን የሥነ-ምግባር ደንብና የዲሲፕሊን እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ተገቢ ሥርዓት የማውጣት ግዴታ አለበት።

## 39. <u>የተማሪዎች ቅበላ</u>

1/ በማንኛውም ተቋም በቅድመ ምረቃ ትምህርት ለመመዝገብ የሚችሉ ተማሪዎች የመሰናዶ ትምህርትን ያጠናቀቁና የዩኒቨርስቲ መግቢያ ፈተናን ያለፉ መሆን ይኖርባቸዋል፤ በውጭ አገር የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን አጠናቀው በሚኒስቴሩ የአቻ ግምት የተሰጣቸው ተማሪዎችም የመመዝገብ ዕድሉን ሊያገኙ ይችላሉ።

2/ የዩኒቨርስቲ መግቢያ ፈተናውን የሚያስተዳድረውና የቅበላ መስፈርቱን የሚወስነው ሚኒስቴሩ ይሆናል።

3/ የዚህ አንቀጽና የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎችና አግባብነት ያላቸው ሌሎች ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማንኛውም ተቋም የሚከተሉትን ተማሪዎች ይቀበላል፤

ሀ) በቅድመ ምረቃ ፕሮግራሙ የመሰናዶ ትምህርትን አጠናቀው የዩኒቨርስቲ መግቢያ ፈተናን ያለፉና በውጭ አገር የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን አጠናቀው በሚኒስቴሩ የአቻ ግምት የተሰጣቸውን፤

ለ) ለሁለተኛ ዲግሪ ትምህርት የቅደመ-ምረቃ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁና ተቋሙ ያስቀመጠውን መግቢያ የቅድመ-ምረቃ ውጤት ያላቸውን፤ ወይም ለሶስተኛ ዲግሪ በሁለተኛ ዲግሪ የተመረቁና ተቋሙ ያስቀመጠውን መግቢያ አካዳሚክ ውጤት ያላቸውን፣

ሐ) ብቃትን መሠረት አድርጎ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ተቋሙ የሚያዘጋጀውን የመግቢያ ፈተናን ያለፉ የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት ምሩቃንን።

4/ የዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ (1) እና (3) ተራ ፊደል (ሀ) ድንጋጌዎች ቢኖሩም ልዩ ድጋፍን ማግኘት ስለሚገባቸው ዜጎች እና የቅበላ ስነ ስርዓቱ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ የሚወሰን ሆኖ ሚኒስቴሩ ደንቡን ለማስፈጸም በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

5) ማንኛውም የመንግስት ተቋም በተቋሙ የመቋቋሚያ ሕግ መሠረት በሚወሰን የቅበላ ሥርዓትና የተቋሙ ሰኔት በሚወስነው አገባብ መሠረት ዓቅሙ ያላቸው ጎልማሶችን በቅድመ ምረቃ ተማሪነት ሊቀበል ይችላል፤ ሚኒስቴሩ ይህን ልዩ

የቅበላ ስርዓትን በግል ተቋማትም ሁኔታው ሲፈቅድ እንዲፈጸም ሊያደርግ ይችላል፡፡

6/ የተማከለ የተማሪዎች ምደባ እስከቀጠለ ድረስ ሚኒስቴሩ ተማሪዎችን የሚመድበው የመንግሥት ተቋማትን በማማከር ይሆናል፤ የመንግሥት ተቋማት ራሳቸው በቀጥታ ተማሪዎችን ለመቀበል የሚችሉበት ጊዜ ሲደርስና ተግባራዊ መደረጉም ሲታመንበት ሚኒስቴሩ የመግቢያ ፈተናውን በማስተዳደር፣ የማለፊያ ነጥብንና መግቢያ ነጥብን በመወሰን፣ ስለ ልዩ ድጋፍ ተጠቃሚዎች መመሪያን በማውጣት እና የቅበላው አፈፃፀምን በመከታተልና በማስተካከል ላይ የተገደበ ይሆናል፡፡

## 40. ስለ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች

1/ ተቋማት አገልግሎት መስጫ አውታሮቻቸውና ፕሮግራሞቻቸው አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ ሆነው እንዲታነጹ የሚቻላቸውን ሁሉ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

2/ ሁኔታና ዓቅም በፈቀደ መጠን ተቋማት ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎቻቸው ጥቅም ሲሉ የክፍሎቻቸውን አጠቃቀምና አመዳደብ መለወጥ፣ አማራጭ የፈተና ሥርዓቶችን መቀየስና የትምህርት ሂደቱን የሚያመቻቹ ዜዴዎችን መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡

3/ የተቋሞች ሕንፃዎች ዲዛይን፣ የግቢዎቻቸው ተፈጥሯዊ አቀማመጥ፣ ኮምፒውተሮቻቸውና ሌሎች የመገልገያ አውታሮቻቸው የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ፍላጐት ግምት ውስጥ ያስገቡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

4/ አስፈላጊ ሲሆንና አቅም በፈቀደ መጠን ተቋማት ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎቻቸው የቱቶሪያል፣ የፈተና ጊዜያት መራዘምና የማስረከቢያ ጊዜያት መራዘምን ጨምሮ ልዩ አካዳሚክ ዕርዳታዎች ሊያደርጉላቸው ይገባል፡፡

## 41. የመማር-ማስተማር ጥራትና የተማሪዎች ምዘና

1/ በማንኛውም ተቋም ውስጥ የሚኖረው የመማር ማስተማር ሂደት የትምህርቱ አሰጣጥ በየትኛውም መልኩ ቢሆን በንቃት መማርን የሚያራምድ መሆን ይኖርበታል፡፡

2/ በማንኛውም ተቋም ውስጥ የሚኖረው የመማር ማስተማር ሁኔታ በተቻለ መጠን በክፍል ውስጥም ሆነ በተቋሙ ግቢዎች ውስጥ ተማሪዎችን ለመማር የሚያበረታታ መልካም ድባብ ያለው መሆን ይኖርበታል፡፡

3/ የትምህርቱ አቀራረጽና አሰጣጥ የተማሪዎችን ዕውቀትና ክህሎት የሚያበለጽግ፣ መልካም እሴቶችን የሚያስታጥቅና በተማሪዎች አመለካከት ላይ አውንታዊ እድገት የሚያመጣ መሆን ይኖርበታል፡፡

4/ ተማሪዎች የሚመዘኑት በመዛኙነቱ አግባብነት ባለው ስርዓትና በተማሩት ላይ ተመሥርቶ መሆን ይኖርበታል፤ የምዘና ውጤት አሰጣጥ ስርዓትም የተረጋገጠውን ብቃት የሚገልፅ ይሆናል፡፡

5/ በተቋም ደረጃ ዕውቅና የተሰጠውና በእያንዳንዱ የትምህርት ክፍል የሚሠራበት እያንዳንዱ የአካዳሚክ ሠራተኛ ሊያከብረው የሚገባ ተማሪዎችም አስቀድመው የሚያውቁት የተማሪዎች ምዘናና ፈተና ስርዓት ይኖራል፡፡

6/ በተማሪዎች ምዘናና ፈተናና የውጤት አሰጣጥ ረገድ አመራር የሚሰጡ በተገቢ የትምህርት ክፍሎች ደረጃ መሪ አካላት እንዲኖሩ ለማድረግ የሚያስችል አደረጃጀት ይኖራል::

7/ ተማሪዎች ስለምዘና ዘዴዎች፣ ስለፈተናዎችና የውጤት አሰጣጥ ስርዓት ወይም ስላገኙት ውጤት የሚያቀርቧቸው ቅሬታዎች አግባብነት ባላቸው የተቋሙ አካላት ተገቢው ትኩረት ተሠጥቷቸው መታየት ይኖርባቸዋል::

8/ አካዳሚክ ሠራተኞች በተማሪዎች ምዘናና ውጤት አሰጣጥ የሥራ ላይ ሙያዊ የንድፈ-ሃሳብና የክህሎት ሥልጠና ይሰጣቸዋል፤ የማስተማር ብቃትና የምዘና ክህሎቶችን በብቃት መተግበር በአካዳሚክ ሰራተኛነት ለመቀጠልና ዕድገትን ለማግኘት እንደ ቁልፍ ቅድመ ሁኔታ ይወሰዳል::

9/ የማስተማር ዘዴዎች፣ የተማሪዎች ምዘና፣ የምዘና ውጤቶችና ደረጃ አሰጣጥን የሚመለከቱ ሥነ-ሥርዓቶች በተቋሙ የሰኔት ደንብ ውስጥ መካተትና በትምህርት ክፍሎች መመሪያዎች ተብራርተው መገለጽ ይኖርባቸዋል::

## ክፍል ሶስት
## የመንግስት ተቋማት

### ንዑስ ክፍል አንድ
### አስተዳደርና ውስጣዊ አደረጃጀት

**42. የመንግስት ተቋማት አደረጃጀት**

1/ የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም የመንግስት ተቋም፣

ሀ) የአመራርና አማካሪ አካላት፣

ለ) የአካዳሚክ ክፍሎች፣

ሐ) እንዳግባቡ የመማሪያ ሆስፒታል አመራር፣

ሐ) የአስተዳደርና የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ ክፍሎች፣

መ) ቢሮዎችና ተግባራቱን በተገቢው ሁኔታ ለማከናወን የሚያስችሉት ሌሎች መገልገያዎች፣

ይኖሩታል::

2/ በዚህ አዋጅ መሠረት የአካዳሚክ ክፍሎችን ለመመስረት ሲወሰን ከትምህርትና ምርምር አግባብነትና ጥራት፣ ከትብብር አሰፈላጊነትና ከውጤታማ የሀብት አጠቃቀም አኳያ እየታየ መሆን ይኖርበታል::

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የተቋቋመ የትምህርት ክፍል በፕሬዚዳንቱ ተዘጋጅቶና በአስተዳደር ካውንስል፣ በዩኒቨርስቲ ካውንስልና በሰኔት የተመከረበትና በቦርዱ የፀደቀ የአስተዳደር ሥርአት ይኖረዋል:: የአስተዳደር ሥርዓቱም የአመራርና የአስፈፃሚ አካላትን የያዘና ኃላፊነታቸውን እንዲሁም የአመራርና የአስተዳደር ሥነሥርአቶችን ያካተተ ይሆናል::

4/ የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች ቢኖሩም፣ የማንኛውም መንግስታዊ ተቋም በቦርዱ የማፀደቅና በሚኒስቴሩም የማስፈቀድ ግዴታ እንደተጠበቀ ሆኖ በአለም አቀፍ መልካም ልምድ ላይ ተመሥርቶ ተልእኮውን ለማሳካት የሚያስችል

የተሻለ ውጤታማ ሥራ ለመስራት ብቻ በማሰብ አደረጃጀቱን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመቀየር እራሱን እንደገና ሊያደራጅ ይችላል::

5/ ሚኒስቴሩ በሌላ አኳኋን እንዲፈፀም መመሪያ ካልሰጠ በስተቀር፣ ማንኛውም ተቋም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት እራሱን እንደገና ለማደራጀት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የተቋሙ ኘሬዚዳንት በአስተዳደር ካውንስል፣ በዩኒቨርስቲ ካውንስል፣ በሰኔትና በተቋሙ የመምህራንና የተማሪዎች ማሕበራት የተመከረበት የተሟላ የውሳኔ ሃሳብ ለቦርዱ ያቀርባል::

## 43. የአመራርና አማካሪ አካላት

1/ ማንኛውም የመንግሥት ተቋም እንደአስፈላጊነቱ የሚከተሉት የአመራርና አማካሪ አካላት ይኖሩታል፤

ሀ) ቦርድ፤

ለ) ኘሬዚዳንት፤

ሐ) ሰኔት፤

መ) የአስተዳደር ካውንስል፤

ሠ) የዩኒቨርስቲ ካውንስል፤

ረ) የትምህርት ክፍል ካውንስል፤

ሰ) የትምህርት ክፍል አስተዳደር ካውንስል፤

ሸ) የዲፓርትመንት ጉባኤ፤

ቀ) በቦርዱ ወይም በሴኔቱ ወይም በዩኒቨርስቲ ካውንስሉ የሚቋቋሙ አስፈላጊ ቁጥርና አይነት ያላቸው አማካሪ ወይም ልዩ ኮሚቴዎች ወይም ካውንስሎች::

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የመንግሥት ተቋም የአመራርና የአማካሪ አካላት አደረጃጀትና ስያሜዎችን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 42 ንዑስ አንቀጽ (3)፣ (4) እና (5) መሠረት ፕሬዚዳንቱ በሚሰጠው ምክር ላይ ተመሥርቶ ቦርዱ ሊለውጣቸው ይችላል::

3/ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) ተራ ፊደል (ረ) እስከ (ሸ) የተመለከቱት የትምህርት ክፍሎች አመራር አካላት ይዘት፣ አመሰራረት፣ ሃላፊነትና የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት በዚህ አዋጅ አንቀፅ 42 ንኡስ አንቀፅ (3) መሰረት ይወሰናል::

## 44. የቦርድ ኃላፊነት

1/ የመንግስታዊ ተቋም ቦርድ የተቋሙ የበላይ አመራር ሆኖ የሚከተለው ኃላፊነት ይኖረዋል፤

ሀ) ተቋሙ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች መተግበሩንና በተቋሙ ውስጥ መልካም አስተዳደር መስፈኑን መከታተልና ማረጋገጥ፤

ለ) የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የተቋሙ እቅድ፣ በጀት፣ የትኩረት አቅጣጫ፣ አደረጃጀት፣ የአስተዳደርና አሰራር ስርዓት፣ የውስጥ ደንብና የአካዳሚክ ፕሮግራሞችን በሚመለከት የሚቀርቡለት ሃሳቦችን መርምሮ ማፅደቅና ተግባራዊነታቸውን መከታተል፤

ሐ) በፕሬዚዳንቱ በሚቀርብ ሃሳብ ላይ በመመሥረት ምክትል ፕሬዚዳንቶችና ሌሎች አካዳሚክ ሃላፊዎች እንዲሁም የሰኔት አባላት እንዳግባቡ የሚታጩበት፣ የሚመረጡበት፣ የሚሾሙበት ወይም የሚመደቡበትን ሥርዓትና የአገልግሎት ዘመናቸውን የሚመለከቱ መመሪያዎችን ማውጣት እና በትክክል መተግበራቸውንም መከታተል፤

መ) ፕሬዚዳንታዊ እጩን ለሹመት እንደአግባብነቱ ለሚኒስትሩ ወይም ለክልሉ አካል ማቅረብ እና ፕሬዚዳንቱ በሚያቀርበው ዕጩዎች መሠረት ምክትል ፕሬዚዳንቶችን መሾም፤

ሠ) አግባብነት ያላቸው ሕጎች ተፈፃሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ምክትል ፕሬዚዳንት ኃላፊነቱን በመወጣት ረገድ ከፍተኛ የሆነ ድክመት ካሳየ ከሃላፊነት ማሰናበትን ጨምሮ የዲሲፕሊን እርምጃ መውሰድ፤ ፕሬዚዳንቱን የሚመለከት ሲሆን ደግሞ ሚኒስትሩን በማማከር እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ፤

ረ) የተቋሙን ኦዲተሮች መሾምና ክፍያቸውን መወሰን፤

ሰ) የተቋሙን የስትራቴጂክ እቅድ፣ አመታዊ እቅድና በጀት ማቅረብና ሲፀድቁም ተፈፃሚነታቸውን መከታተል፤ የተቋሙን የክንውን ሪፖርትና የፋይናንስ መግለጫን ማፅደቅና ማቅረብ፤

ሸ) ተቋሙ የዋና ዋና እና የጥቃቅን ገቢዎቹን ትክክለኛ የሂሳብ መዝገብ መያዙንና ወጪዎቹ በበጀቱ መሠረት መሆናቸውን መከታተልና ማረጋገጥ፤

ቀ) የተቋሙ ሌሎች የአመራር አካላት ከባድ የሕግ መጣስ ተግባር በሚፈፅሙበት ጊዜ ወይም ከባድ የሆነ የገንዘብ ብክነት ሰለመከሰቱ ጥርጣሬ ካለ ወይም በርግጥ ተከስቶ ከሆነ በራሱ ስልጣን ክልል ተገቢውን የመፍትሔ እርምጃ መውሰድና ወዲያውኑ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ማቅረብ፤

በ) በፌደራል መንግስት የሰራተኞች አዋጅና ደንቦች መሠረታዊ መርሆዎች ላይ በመመሥረት የአስተዳደርና የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን ቅጥር፣ እድገት፣ ዲሲፕሊን፣ ደሞዝ እና ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን የሚመለከት ፖሊሲን እንዳስፈላጊነቱ እንዲዘጋጅ ማድረግና ማፅደቅ፤

ተ) ተቋሙን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ መረጃ የመጠየቅና የማግኘት እና ለሚኒስቴሩ የሚያስፈልግ ከሆነም ሪፖርት ማድረግ፤

ቸ) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በተቋሙ ማቋቋሚያ ሕግ ላይ የማሻሻያ ሃሳብ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ፤ ለከፍተኛ ትምህርት ዕድገት በሚጠቅሙ ማናቸውም ጉዳዮች ላይ በአጠቃላይና የተቋም አስተዳደር ላይ በተለይ በተቋም መሪነቱ ከሚያስተውለው ወይም ከሚያውቀው በመነሳት ለሚኒስቴሩ ምክር መስጠት፤

ኀ) በመንግስታዊ ተቋሙ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ሲቀርብ መመርመርና የመጨረሻ ውሳኔ መስጠት፤

ነ) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) ተራ ፊደል (ኀ) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ተቋሙ ቅሬታዎችን በተፋጠነ መንገድ ተቀብሎ የሚፈታበት የተሟላ ተቋማዊ ሥርአት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ፤

ኘ) የተቋሙን፣ የተቋሙን አካዳሚክ ክፍሎች፣ የመሪዎቹንና የአስተዳደር አካላቱን የስራ አፈፃፀም በፕሬዚዳንቱ ሪፖርት መሰረት ከእቅድ አኳያ መገምገም፤

ሰ) የሰኔት ውሳኔዎችና የሚያወጣቸው የአካዳሚክ ሕጎች መፈፀማቸውን መከታተል፤

ከ) በኘሬዚዳንቱ ወይም በሰኔት የተላለፉ ውሳኔዎች የተቋሙን ተልእኮ የሚጎዱ ወይም የመንግስትን ፖሊሲ፣ ይህንን አዋጅ ወይም ሕገመንግስቱን የሚቃረኑ ሆነው ሲገኙ ውሳኔዎቹን መሻር፤

ኸ) የራሱን የአሰራር ሥነሥርዓትና የውስጥ አስተዳደር ደንብና አባላቱን የሚመለከት የዲሲፕሊን ደንብን ማውጣት፤

ወ) የኘሮፌሰርነት የማዕረግ ዕድገትን ማፅደቅ፤

ዐ) ከኘሬዚዳንቱ በሚቀርብ ምክር ላይ ተመሥርቶ ተቋሙ ለትምህርት የሚያስከፍላቸውን የተለያዩ ክፍያዎች አይነትና መጠን እና የሚኒስትሮች ምክር ቤት በወሰነው መሠረት የተቋሙን ገቢ ግምት ውስጥ በማስገባት የተለያዩ ተከፋይ አበሎችን፣ የትርፍ ሰዓት ክፊያዎችንና የመሳሰሉትን መወሰን፤

ዘ) የሰኔቱን፣ የአስተዳደር ካውንስሉንና የዩኒቨርስቲ ካውንስሉን በትክክል መደራጀትና መሥራት መከታተል፤ አስፈላጊነቱን ሲያምንበትና በፕዚዳንቱ ምክር ላይ በመመሥረት ተጠሪነቱ ለኘሬዚዳንቱ የሆኑ ልዩ አማካሪ አካላትን ማቋቋም፤

ዠ) በዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎችና በተቋሙ ማቋቋሚያ ሕግ የተሰጠው ሌላ ኃላፊነትን መወጣትና ይህን አዋጅ ማክበርና ተቋሙም እንዲያከብረው ማድረግ::

2/ የቦርዱ ተጠሪነት እንዳግባቡ ለሚኒስቴሩ ወይም ለተገቢው የክልል መንግስት አካል ይሆናል::

3/ የፌደራል መንግስት ተቋም የቦርድ ሰብሳቢ በሚኒስትሩ የሚሾም ሆኖ ቦርዱ የተሰጠውን ሃላፊነት በትክክል መወጣቱን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት::

4/ የፌደራል መንግስት ተቋም ቦርድ አባላት ጥቅማ ጥቅሞች በሚኒስቴሩ የሚወሰኑና በተቋሙ የሚሸፈኑ ሆኖ የተቋሙን ዓቅም ግምት ውስጥ ያስገቡ ይሆናሉ::

**45. <u>ስለቦርዱ አባላትና ምልአተ ጉባኤ</u>**

1/ ቦርዱ ሰብሳቢውን ጨምሮና ዓቅምን መሰረት ያደረገ የሴቶች ተሳትፎ ያለበት ሰባት ድምፅ መስጠት የሚችሉ አባላት ይኖሩታል::

2/ ሚኒስትሩ ከቦርዱ ሰበሳቢ በተጨማሪ ሶሰት ድምፅ መስጠት የሚችሉ የቦርድ አባላትን መርጦ ይሾማል::

3/ ኘሬዚዳንቱ ከአስተዳደር ካውንስሉና ከሴኔቱ ጋር በመመካከር ሌሎች ሶስት እጩዎችን በሚኒስትሩ እንዲሾሙ ያቀርባል::

4/ የተቋሙ ኘሬዚዳንት ድምፅ የማይሰጥ የቦርዱ አባልና ፀሃፊ ይሆናል::

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) መሠረት የሚሾሙት የቦርድ አባላት በኃላፊነት ቦታዎች ላይ ያሉ ወይም ያገለገሉና በተለይ በማስተማር ወይም በምርምርና በግል ብቃታቸው የታወቁ ግለሰቦች፣ ወይም እውቀታቸው፣ ልምዳቸውና አትኩሮታቸው ለከፍተኛ ትምህርት አላማዎች በአጠቃላይና

ለተቋሙ ተልእኮዎች መሳካት በተለይ አስተዋፅኦ ለማበርከት የሚያስችላቸው የተቋሙ ምርትና አገልግሎት ተጠቃሚዎች ተወካዮች መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

6/ ቦርዱ በራሱ ውሳኔ ማንኛውንም ሰው በአስረጂነት በስብሰባዎቹ ሊያሳትፍ ይችላል፡፡

7/ አምስት ድምፅ የሚሰጡ የቦርዱ አባላት ሲገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፡፡ ሆኖም አምስት የቦርድ አባላት መሳተፍ የማይችሉበት አስቸጋሪ ሁኔታ ከተፈጠረ ቦርዱ በአራት አባላት ምልአተ ጉባኤ ስብሰባዎቹን ያካሄዳል፡፡ ቦርዱ ይህንን ሁኔታ በተመለከተ በአሰራር ሥነሥርዓት ደንቡ ላይ በግልፅ ይደነግጋል፡፡

8/ የቦርዱ ሰብሳቢ ጊዜ በተቆረጠለት ስብሰባ ላይ መሳተፍ የማይችል ከሆነ በስብሰባው ላይ የተገኙ አባላት ያንን ስብሰባ የሚመራ ሰብሳቢ ከመካከላቸው በመምረጥ የስብሰባውን አጀንዳ ይፈጽማሉ፡፡

9/ ቦርዱ በጉዳዮች ላይ ውሳኔ የሚያሳልፈው በአብላጫ ድምፅ ይሆናል፡፡

## 46. ስለቦርዱ መደበኛ ስብሰባዎች

1/ ቦርዱ በአመት ከሦስት እስከ አራት የሚሆኑ መደበኛ ስብሰባዎችን ያደርጋል፤ ቦርዱ ባጠቃላይ ሃላፊነቱን ለመወጣት እንዲችልና በተለይ የእቅድና የበጀት ዝግጅቶች እንዲሁም አፈጻጸም ላይ አስተዋፅኦ ለማድረግ እንዲችል መደበኛ ስብሰባዎቹ አመቺ በሆኑ ወቅቶች እንዲካሄዱ ያደርጋል፡፡

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ በሰብሳቢው ጥሪ ወይም ድምፅ የመስጠት መብት ካላቸው አባላቱ አንድ ሶስተኛው በሚጠይቁበት ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ማድረግ ይችላል፡፡

3/ ፕሬዚዳንቱ የቦርዱ ሰብሳቢ ስምምነትን በማግኘት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ማድረግ ይችላል፤ ሁሉም የቦርዱ ስብሰባዎች በቂ ዝግጅት የተደረገባቸው መሆኑን፣ በበቂ ሁኔታ በሰነድ መያዛቸውን፣ ሰነዶቹ በጥንቃቄ መጠበቃቸውን እና ቦርዱ በሚያዘው መሠረት ውሳኔዎቹ በትክክል ለሚመለከታቸው መተላለፋቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

## 47. የቦርድ አባልነት መቋረጥ

የቦርድ አባልነት በሚከተሉት ምክንያቶች ሊቋረጥ ይችላል፤

1/ ሚኒስቴሩ በሚወስነው መሠረት የአገልግሎት ዘመን ሲያበቃ፤

2/ በፈቃደኝነት ከአባልነት በመልቀቅ፤

3/ በሞት፣ በሕመም ወይም በከባድ ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ በመገኘት፤

4/ በከባድ ጥፋት፣ በችሎታ ማጣት ወይም ስብሰባዎች ላይ ለመገኘት ከባድ የሆነ ድክመት በማሳየት ወይም ባለመቻል፤

5/ ሚኒስቴሩ ቦርዱን ሙሉ በሙሉ ለመቀየር ወይም በከፊል ለመለወጥ ውሳኔ ላይ ሲደርስ፡፡

## 48. ስለቦርድ የሥራ አፈፃፀም ግምገማ

1/ ቦርዱ አመራሩን በቀጣይነት ለማሻሻል የሚረዱ ትምህርቶችን ለማግኘት የራሱን የሥራ አፈፃፀም ግምገማ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

2/ የቦርዱ የአፈፃፀም ግምገማ ኘሬዚዳንቱ ተሳትፎ በሚያደርግበት ድምፅ የመስጠት መብት ባላቸው አባላት በዝግ ስብሰባ ይካሄዳል::

3/ የቦርዱ ሰብሳቢ የግምገማውን ውጤቶች በየወቅቱ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ያደርጋል፤ የቦርድ ሰብሳቢዎችና የትምህርት ሚኒስቴር መደበኛ የጋራ መድረክም በዓመት ሁለት ጊዜ ይኖራል::

4/ ቦርዱ ግምገማውን መቼና እንዴት እንደሚያካሂድ ይወስናል፤ ሆኖም በአመት ቢያንስ አንድ የክትትል ግምገማና አንድ የማጠቃለያ ግምገማ ማድረግ ይኖርበታል::

## 49. ስለሴኔት

የቦርዱ ሃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሴኔት የአካዳሚክ ጉዳዮችን በሚመለከት መሪ አካል በመሆን የሚከተለው ሃላፊነት ይኖረዋል፤

1/ የተቋሙን የትምህርት ዘመን መወሰን፤

2/ የተቋሙን አካዳሚክ ፕሮግራሞችንና ስርዓተ ትምህርቶቻቸውን መወሰን፤ የትምህርት ክፍሎች የሚሰጡትን ትምህርት እና የሚያካሂዱትን ምርምር ጥራትና አግባብነት ለማረጋገጥ እንዲችሉ መምራትና አቅጣጫን ማስያዝ፤

3/ በዚህ አዋጅ መሠረት የትምህርትና ምርምር ፕሮግራሞችን በሚመለከትና የአካዳሚክ ማሕበረሰቡ የሚተዳደርበትን ደንብ ማውጣትና ስለ መከበሩም መከታተል፤

4/ ዲግሪ የሚሰጥበትን ወይም የሚሰረዝበትን ሁኔታዎችን መወሰን፤

5/ ተቋም አቀፍ የትምህርት አግባብነትና ጥራት ማጎልበቻና የተማሪዎች ምዘና ስርዓትን ማውጣት፤

6/ በአካዳሚክ ሃላፊነት ስለሚሹሙት ጥያቄ ሲቀርብለት ለፕሬዚዳንቱ ምክር መስጠት፤

7/ የፕሮፌሰር ማዕረግ ዕድገት ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ደግፎ ለቦርዱ ማቅረብና በተባባሪ ፕሮፌሰር ዕድገት ላይ የመጨረሻውን ውሳኔ መስጠት፤

8/ በትምህርት ክፍሎች በሚቀርብ በፕሮፌሰር ደረጃ የሚፈፀም የአዲስ ቅጥር ጥያቄ ላይ መወሰን፤

9/ የሴኔት ኮሚቴዎች ብዛት፣ አባልነት፣ ሃላፊነትና አሰራርን መወሰን፣

10/ በፕሬዝዳንቱ በሚቀርበው የውሳኔ ሃሳብ መሠረት በተቋሙ እውቅና ሊሰጣቸው የሚገባ ልዩ አስተዋፅኦ ላስመዘገቡ ሰዎች የክብር ዲግሪ ወይም ሌሎች ሽልማቶችን መስጠት፤

11/ በተቋሙ ሥር ስላሉት የትምህርት ክፍሎች መክፈት፣ መዝጋት፣ የስም ለውጥ ወይም መዋሃድ በኘሬዝዳንቱ በሚቀርብለት የውሳኔ ሃሳብ መሠረት መርምሮ ማፅደቅ::

12/ በተቋሙ ማቋቋሚያ ሕግ የሚሰጠውን ሌላ ሃላፊነት ወይም በፕሬዚዳንቱ የሚመራለትን ጉዳይ ማከናወን::

## 50. የሴኔት አባላት

1/ የሰኔት የአባልነት ሁኔታ፣ የአገልግሎት ዘመን እና የአባላት ቁጥር በተቋሙ ማቋቋሚያ ሕግ ይወሰናል::

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ከሰኔቱ አባላት ቢያንስ አብላጫው በፕሬዝዳንቱ የሚመረጡ ሆነው ለሃላፊነቱ የሚመጥኑና በተቋሙ ውስጥ በተነፃፃሪ ረጅም አገልግሎት ያላቸው የአካዳሚክ ሠራተኞች ይሆናሉ::

3/ ኘሬዝዳንቱ የተቋሙ የአካዳሚክ ማሕበረሰብ በተገቢ ሁኔታ በሰኔቱ ውስጥ መወከሉን ያረጋግጣል፤ የሰኔቱ ስብሰባዎችን በሰብሳቢነት ይመራል::

4/ ለአፈፃፀም ውጤታማነት ሲባል በሰኔቱ አባልነትና የአባላት ብዛትን እዲሁም የስራ ዘመን ለውጥ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በፕሬዚዳንቱ ምክር መሰረት ቦርዱ ማሻሻያ ማድረግ ይችላል::

## 51. የሰኔት ስብሰባዎች

1/ ሰኔት የአባላቱን ዲስፐሊን ጨምሮ የራሱን መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች በሚያወጣው የውስጥ ደንብ ይወስናል::

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም ፕሬዝዳንቱ ሲጠይቅ ሰኔቱ ቀጣይ ስብሰባ ሊያካሂድ ይችላል::

3/ ሰኔቱ ፕሬዚዳንቱ ወይም ቦርዱ ሲጠይቅ ወይም ከአባላቱ አንድ ሶስተኛው ሲጠይቁ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያካሂድ ይችላል::

4/ ፕሬዚዳንቱ የሰኔት ስብሰባዎች በበቂ ሁኔታ ዝግጅት የተደረገባቸው መሆኑን፣ በበቂ ሁኔታ መዘገባቸውንና ቃለ ጉባኤዎቹ መጠበቃቸውን፣ በጉዳዮች ላይ የሚደረገው ውይይት ሁሉንም የዳሰሰ መሆኑን እና የሰኔት ውሳኔዎች ለሚመለከታቸው በትክክል መተላለፋቸውንና መተግበራቸውን ያረጋግጣል::

5/ ከሰኔት አባላት ከግማሽ በላይ በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፤ የሰኔት ውሳኔዎች በአብላጫ ድምጽ ይተላለፋሉ፤ ደምጽ እኩል በእኩል ከተከፈለም ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል::

6/ ሰኔት በሃላፊነቱ መሰረት የትምህርት ክፍሎችን፣ የኮሚቴዎቹን እና እንደ አካል የራሱን የሥራ አፈፃፀም ይገመግማል፤ የግምገማው ውጤት በኘሬዚዳንቱ አማካኘነት ለቦርዱ ይቀርባል::

7/ ሰኔቱ በማንኛውም ስብሰባው ለስራ አስፈላጊ ናቸው ያላቸው የስራ ክፍሎችን ወይም ግለሰቦችን በአስረጂነት ሊያሳትፍ ይችላል::

## 52. ስለመንግሥት ተቋም ኘሬዚዳንትና ምክትል ኘሬዚዳንት ሹመትና የስራ አፈፃፀም ግምገማ

1/ የተቋም ኘሬዚዳንት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ (1) ተራ ፊደል (መ) መሠረት ቦርዱ አወዳድሮ ከሚያቀርባቸው እጩዎች መካከል እንደአግባቡ በሚኒስትሩ ወይም በሚመለከተው የክልል አካል ይሾማል::

2/ የኘሬዚዳንትነት የሃላፊነት ቦታ በቦርዱ በሚሰየም አካል በይፋ ለተወዳዳሪዎች ይገለጻል::

3/ የመንግሥት ተቋም ምክትል ኘሬዚዳንቶች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ (1) ተራ ፊደል (ሐ) እና (መ) መሠረት በይፋ ተወዳዳሪዎች ተጋብዘው የተሻለ ብቃትና ዝግጁነት ያለው ተመርጦ በቦርድ ይሾማል::

4/ የመንግሥታዊ ተቋም እጩ ኘሬዚዳንትና ምክትል ኘሬዚዳንቶች የአካዳሚክ መሪነት እና የአስተዳደር ክህሎት ያላቸው እንዲሁም ለተቋማዊ ለውጥና እድገት ዝግጁ የሆኑና ሕገ መንግሥቱንና የመንግሥት ፖሊሲዎችን የተቀበሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

5/ የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (4) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የውድድርና የምርጫ ሥነ ሥርዓት ዝርዝር መመሪያ በተቋሙ ማቋቋሚያ ሕግና በቦርዱ ይወጣል፡፡

6/ የመንግሥት ተቋም ኘሬዚዳንት የሥራ ዘመን ስድስት አመት ሲሆን የምክትል ፕሬዚዳንት አራት አመት ይሆናል፤ ሆኖም የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በተደጋጋሚ ሊሾሙ ይችላሉ፡፡

7/ ቦርዱ የኘሬዚዳንቱንና የምክትል ኘሬዚዳንቶቹን የሥራ አፈፃፀም የክትትል ግምገማ በዓመት ሁለት ጊዜ እንዲሁም ጥልቀት ያለው ግምገማ ደግሞ በየሶስት አመቱ ኘሬዚዳንቱና ምክትል ኘሬዚዳንቶቹ በተገኙበትና ያለድምፅ በሚሳተፉበት ሁኔታ ያካሂዳል፡፡

8/ ማንኛውም ሰው ከ180 ቀናት በላይ ተጠባባቂ ኘሬዚዳንት ወይም ተጠባባቂ ምክትል ኘሬዚዳንት ሆኖ መቆየት የለበትም፡፡

## 53. የመንግስት ተቋም ኘሬዚዳንት ኃላፊነት

1/ የቦርዱ ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግስት ተቋም ኘሬዚዳንት የተቋሙ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን የሚከተሉት ሃላፊነቶች ይኖሩታል፤

ሀ) ተቋሙ የሥራ ድርሻውንና ተልዕኮውን ለማሳካት ይችል ዘንድ ተቋሙን ይመራል፣ ያስተዳድራል፤

ለ) የተቋሙ አካላትና ማሕበረሰብ የከፍተኛ ትምህርት አላማዎችንና የተቋሙን መሪ እሴቶች ማክበራቸውን ያረጋግጣል፤

ሐ) የዚህ አዋጅና የሌሎች በተቋሙ ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑ አግባብነት ያላቸው ሕጐች ድንጋጌዎች መከበራቸውን ያረጋግጣል፤

መ) ተቋሙ በቅበላ ዓቅሙ መሰረት አገሪቱ በምትፈልገው ሙያዊ ስብጥርና ጥራት ወይም ብቃት ያላቸው ምሩቃንን ማፍራቱን ያረጋግጣል፤

ሠ) መማር ማስተማርንና ምርምርን የሚያበረታታ አመቺ ተቋማዊ ሁኔታን ይፈጥራል፤ በቀጣይነት ይገነባል፤

ረ) የተቋሙ የምርምርና የማማከር ተግባራት ሁሉ ቅድሚያ በሚሰጣቸው አገራዊ ጉዳዮች ላይ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤

ሰ) ተቋሙ ተልእኮውን ለማሳካት ከአለም አቀፍ እንዲሁም ከፌዴራልና ከክልል ተቋማት፣ አግባብነት ካላቸው ኤጀንሲዎች እና ከንግድና ኢንዱስትሪ ድርጅቶችና ማሕበራት ጋር በዘላቂነት ትስስር እንዲኖረው ያደርጋል፤

ሸ) ተቋሙ ሁልጊዜም ከሃገራዊና አለም አቀፋዊ እድገቶች ጋር እኩል የሚራመድና በትምህርት፣ በስልጠና፣ በምርምር፣ በማማከር እና በማሕበረሰብ አገልግሎቶች የአገሪቱን ፍላጎት ለማርካት በሚያስችለው ደረጃ የሚገኝ መሆኑን ያረጋግጣል፤

ቀ) ተቋሙ በሰው ሃይሉ፣ በአደረጃጀቱና አሰራሩ ለተቋሙ ተልዕኮ የሚመጥን ብቃት ያለው የውስጥ አመራርና አስተዳደር ሥርአት እንዲኖረው ያደርጋል፤

በ) የአካዳሚክ ሃላፊዎችና የሴኔት አባላትን የአሰያየምና የሹመት ስርአትን በማዘጋጀትና በቦርዱ በማፀደቅ በተግባር ላይ ያውላል፤

ተ) በትምህርትና ምርምር አግባብነትና ጥራት፣ በተቋማዊ ነፃነትና ተጠያቂነት፣ በአገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማነትና እና በወጪ ቆጣቢነት መርሆች ላይ በመመሥረት የትምህርት ክፍሎች አደረጃጀትን ለሴኔቱና ለቦርዱ አቅርቦ ያስወስናል፤ ሲፈቀድም በተግባር ላይ ያውላል፤

ቸ) የቅጥርና ሃላፊነት ቦታዎች በውድድር የሚያዙ መሆኑንና ከሃላፊነት መነሳትም በስራ አፈፃፀም ግምገማ፣ በዲስፕሊን ጉዳይ እና በአገልግሎት ዘመን ማብቃት ብቻ ላይ ተመሥርቶ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

ኀ) የተቋሙ የትኩረት አቅጣጫ፣ ደንብና መመሪያዎች እና የአሠራር ሥርአት አግባብነት ባለው የመንግስት ፖሊሲ፣ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና አግባብነት ባለው ሌላ ሕግ መሰረት መቀረጻቸውን ያረጋግጣል፤

ነ) ተቋማዊ የደረጃ መለኪያዎችን ያዘጋጃል፤ የተቋሙ የአካዳሚክና የአስተዳደር ሥራዎች በወጡት መለኪያዎች መሠረት መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፤

ኘ) የተቋሙን ገቢና ወጪ በትክክል የሚያሳዩ የሂሳብ መዛግብት መያዛቸውን ያረጋግጣል፤

አ) የቦርድ፣ የሴኔት፣ የአስተዳደር ካውንስል እና የዩኒቨርስቲ ካውንስል ሰብሰባዎች በበቂ ዝግጅትና ወቅታቸውን ጠብቀው እንዲካሄዱ ያደርጋል፤

ከ) በተቋሙ ውስጥ ወይም በተቋሙና በሶስተኛ ወገኖች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችን የተቋሙን ተልዕኮና ጥቅሞች ከማሳካት አኳያ በሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ እንዲፈቱ ያደርጋል፤

ኸ) የተቋሙ እንቅስቃሴና መሠረታዊ ግንኙነቶች በተገቢው የመረጃ ስርዓት መመዝገባቸውን፣ መረጃው ባግባቡ መጠበቁንና አግባብነት ላላቸውም ተደራሽ መሆኑን ያረጋግጣል፤

ወ) የተቋሙን እቅድና በጀት ያዘጋጃል፤ ሲፀድቁም ያስፈፅማል፤

ዐ) ቦርዱ፣ የተቋሙ ማሕበረሰብ፣ መንግስትና ሕዝብ ስለተቋሙ ሁኔታ ወቅቱን የጠበቀ መረጃ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

ዘ) በተቋሙ ምድረ ግቢ ህይወትና ንብረትን ለመጠበቅ የሚያስችል አስተማማኝ የአደጋ መከላከያና የጥበቃ ሥርአት እንዲገነባ ያደርጋል፤

ዠ) ተቋሙ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርገው ማናቸውም ግንኙነት ተቋሙን ይወክላል፤

የ) በተቋሙ ስም የባንክ ሂሳብ ይከፍታል፣ ያንቀሳቅሳል፤

ደ) እንዳስፈላጊነቱ ለምክትል ፕሬዚዳንቶች እና አግባብነት ላላቸው የአካዳሚክ ክፍሎች ሃላፊዎች ሃላፊነቱን በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

ጀ) የውጪ ጉዞዎቹን በታቀዱና ለተቋሙ ባላቸው ፋይዳ ላይ የተመሰረቱ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

ጠ) በተቋሙ ማቋቋሚያ ሕግ እና በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

2/ ኘሬዚዳንቱ ሙሉ የስራ ጊዜውን ለቢሮው ስራዎች ያውላል፤ ለአገልግሎቱ ተገቢውን ደሞዝና ጥቅማጥቅሞች ያገኛል፡፡

3/ ኘሬዚዳንቱ በሁኔታዎች አስገዳጅነት ሥራው ላይ በማይገኝበት ጊዜ እንደ ቋሚ አሰራር የአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንቱ እሱን ተክቶ እንዲሠራ ይወክላል፤ የአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንቱም የማይገኝ ቢሆን ግን ሌላ ምክትል ፕሬዚዳንትን ሊወክል ይችላል፡፡

## 54. የመንግስት ተቋም ምክትል ኘሬዚዳንት ሃላፊነት

1/ በተቋሙ ማቋቋሚያ ሕግ የሚሰጠው ሃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የመንግስት ተቋም ምክትል ኘሬዚዳንት የሚከተለው ሃላፊነት ይኖረዋል፡፡

ሀ) ፕሬዚዳንቱን ሃላፊነቱን ይወጣ ዘንድ ማማከርና ማገዝ፤

ለ) በኘሬዚዳንቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ማከናወን፡፡

2/ ማንኛውም የመንግስት ተቋም ቦርዱ እንደሁኔታው ከሚኒስቴሩ ወይም ከሚመለከተው የክልል አካል ጋር በመመካከር አስፈላጊ ናቸው ብሎ የሚወስነውን ያክል ምክትል ኘሬዚዳንቶች ይኖሩታል፡፡

3/ ምክትል ኘሬዚዳንቶች አብዛኛው የሥራ ጊዜያቸውን ለቢሮው ስራዎች ያውላሉ፤ ለአገልግሎታቸውም ተገቢውን ደሞዝና ጥቅማጥቅሞችን ያገኛሉ፡፡

4/ በማንኛውም የመንግስት ተቋም ውስጥ ተባባሪ ምክትል ኘሬዚዳንት የሚባል አይኖርም፡፡

## 55. ስለኘሬዚዳንትና ምክትል ኘሬዚዳንት አገልግሎት መቋረጥ

1/ የመንግሥት ተቋም ኘሬዚዳንት ወይም ምክትል ኘሬዚዳንት ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ከሃላፊነቱ ሊሰናበት ይችላል፤

ሀ) በፈቃዱ ሥራ በመልቀቅ፤

ለ) በችሎታ ማጣት፣ በከባድ ጥፋት፣ በጽኑ ሕመም ወይም በሞት ምክንያት የተሰናበተ ከሆነ፤

ሐ) በፈቃድ ከ180 ተከታታይ ቀናት በላይ ከሥራ ከተለየ፤

መ) ያለፈቃድ ከ45 ተከታታይ ቀናት በላይ ከሥራ ከተለየ፤ ወይም

ሠ) የአገልግሎት ጊዜው ሲያበቃ፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሠረት ከቦርድ በሚቀርብለት ሃሳብ መሠረት ወይም የቦርዱ ሃሳብ ባይቀርብም ተገቢ እርምጃ ነው ብሎ ካመነ እንዳግባቡ ሚኒስትሩ ወይም የሚመለከተው የክልል አካል ኃላፊ ፕሬዝዳንቱን ከሥራ ማሰናበት ይችላል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሠረት ቦርዱ ምክትል ፕሬዚዳንትን ከሃላፊነት ሊያሰናብት ይችላል፡፡

4/ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በሶስት ተከታታይ የክትትል ወይም በአንድ ጥልቅ የስራ አፈፃፀም ግምገማው የፕሬዚዳንቱ ወይም የምክትል ፕሬዚዳንቱ በሃላፊነት መቀጠል ተቋሙን ይጎዳል ብሎ ቦርዱ ካመነ

እንዳግባብነቱ ከሃላፊነቱ እንዲሰናበት እርምጃን ሊያስወስድ ወይም ሊወስድ ይችላል::

**56. የአስተዳደር ካውንስል**

1/ ፕሬዚዳንቱ ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሃላፊዎች ለመጨመር ያለው ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ፕሬዚዳንቱ፣ ምክትል ፕሬዚዳንቶቹ እና የተቋሙ አጠቃላይ ተማሪዎች ጉዳይ ሃላፊ የአስተዳደር ካውንስሉ ዋናዎቹ አባላት ይሆናሉ፤ የአስተዳደር ካውንስሉ ሰብሳቢ ፕሬዚዳንቱ ይሆናል::

2/ የአስተዳደር ካውንስሉ በስትራቴጂክ ጉዳዮችና ፕሬዚዳንቱ በጋራ መታየት አለባቸው ብሎ በሚያምንባቸው ሌሎች ጉዳዮች ላይ ፕሬዝዳንቱን ያማክራል፤ እንዲሁም የተቋሙን እንቅስቃሴዎች የመከታተያ፣ የማስተባበሪያና የመገምገሚያ መድረክ ሆኖ ያገለግላል::

3/ የአስተዳደር ካውንስሉ ቢያንስ በወር ሁለት ጊዜ በመደበኛነት በታወቀ ቀንና ሰዓት መሠረት መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል::

4/ የአስተዳደር ካውንስሉ ስብሰባዎቹን የሚያካሂደው ከመደበኛ አባላቱ መካከል አብዛኛዎቹ በተገኙበት መሆን ይኖርበታል::

5/ የአስተዳደር ካውንስሉ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ፕሬዚዳንቱ በሚመድበው ፀሐፊ መያዝ ይኖርበታል::

6/ ፕሬዚዳንቱ በአስተዳደር ካውንስሉ ስብሰባዎች ሃሳብ በግልፅና በነፃ መንሸራሸሩን ያረጋግጣል፤ የሃሳብ ልዩነት የተንፀባረቀ ከሆነ የተፎካካሪ ሃሳቦቹን የተቀባይነት ክብደት ለማየት ሲባል ብቻ ፕሬዚዳንቱ በጉዳዩ ላይ ድምጽ እንዲሰጥ ሊያደርግ ይችላል::

7/ በፕሬዚዳንቱ ወይም በሱ በተወከለ ሌላ ሰው ካልሆነ በስተቀር ሌላ አባል ልዩነቶች ሲኖሩ የአስተዳደር ካውንስሉን ውይይትና ውጤት ለሶስተኛ ወገን መግለጽ አይችልም::

8/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች በግል ተቋማት ላይም እንዳግባብነቱ ተፈጻሚ ይሆናሉ::

**57. የዩኒቨርስቲ ካውንስል**

1/ የዩኒቨርስቲ ካውንስል በፕሬዚዳንቱ ሰብሳቢነት የሚመራ ሆኖ፣ አባላቱ የአስተዳደር ካውንስሉ ዋናዎቹ አባላት፣ የአካዳሚክ ክፍሎች ሃላፊዎች፣ የሴኔት ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ የቤተመጻሕፍት ዋና ሃላፊ፣ ሬጅስትራር፣ ሌሎች ቁልፍ የአካዳሚክ መኮንኖች፣ የአገልግሎት ሰጪ ክፍሎች ሃላፊዎች እና በፕሬዚዳንቱ ምክር ላይ ተመሥርቶ ቦርዱ በሚወስነው መሠረት የጾታ ተዋጽኦው የጠበቀ የአካዳሚክ ሠራተኞችና የተማሪዎች ተወካዮች ይሆናሉ::

2/ የዩኒቨርስቲ ካውንስል በተቋሙ ረቂቅ እቅድ፣ በጀት፣ አደረጃጀትና መመሪያዎች፣ የትምህርት ፕሮግራሞች፣ የትብብርና የግንኙነት ስምምነቶች፣ በትምህርት ክፍሎች መከፈል፣ ውህደት፣ የስም ለውጥና መዘጋት እና በተቋሙ የአፈፃፀም ሪፖርቶች ላይ ሃሳብ በመስጠት ፕሬዚዳንቱን ያማክራል::

3/ የዩኒቨርስቲ ካውንስል መደበኛ የስብሰባ ቀንና ሰዓት ኖሮት ቢያንስ በስድስት ወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል::

4/ በዩኒቨርስቲ ካውንስል ስብሰባ ላይ የአባላቱ መገኘት ግዴታ ነው፤ በፕሬዚዳንቱ ፈቃድ መሠረት ካልሆነ በስተቀር አባልነት በውክልና ሊሰጥ አይቻልም፤ ስብሰባዎች ያለምልዓተ ጉባኤ ሊካሄዱ ይችላሉ::

5/ ፕሬዚዳንቱ በዩኒቨርስቲ ካውንስሉ ስብሰባ ሂደት ሃሳብን በነፃ ለመግለፅ የሚያበረታታ ዲሞክራሲያዊ ሁኔታ መኖሩን ያረጋግጣል፤ በካውንስሉ ውይይት ሰፊ የሃሳብ ልዩነት የተንፀባረቀ ከሆነ የሃሳቦቹ ክብደትን ለማወቅ ሲባል ፕሬዚዳንቱ በጉዳዩ ላይ ድምጽ እንዲሰጥ ሊያደርግ ይችላል::

6/ የአስተዳደር ካውንስሉ ፀሃፊ ድምፅ የማይሰጥና በውይይቱ ላይ የማይሳተፍ ፀሃፊ ሆኖ ለዩኒቨርስቲ ካውንስሉም ያገለግላል::

7/ ፕሬዚዳንቱ ወይም ፕሬዚዳንቱ ከሰየመው ሰው ውጪ ማንኛውም አባል የዩኒቨርስቲ ካውንስሉ ቃል አቀባይ ሆኖ ሊያገለግል አይችልም::

8/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የዩኒቨርስቲ ካውንስል የራሱን የአሰራር ደንብ ሊያወጣ ይችላል::

9/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንዳግባቡ በግል ተቋማትም ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ::

## 58. <u>*የመንግሥት ተቋማት የምክክር መድረክ*</u>

1/ የመንግሥት ተቋማት ጥረቶቻቸውን ለማስተባበር፣ የትምህርት መለኪያዎችንና አሰራሮችን ለማመሳሰል፣ የልምድ ልውውጥ ለማድረግ እና ሚኒስቴሩን በከፍተኛ ትምህርት ሃገራዊና አለምአቀፋዊ የስትራቴጂ ጉዳዮች፣ ዕድገትና ሁኔታዎች ላይ ለማማከር በዚህ አዋጅ ዕውቅና የተሰጠው የምክክር መድረክ ሊያቋቁሙ ይችላሉ::

2/ የመንግሥት ተቋማት የምክክር መድረክ በዚህ አዋጅ መሰረት መመስረቱን በሚኒስቴሩ ከተረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ ይፋ እንቅስቃሴ ያደርጋል::

3/ የመንግስት ተቋማት ፕሬዚዳንቶች ተቋሞቻቸውን በመወከል የምክክር መድረኩ አባላት ይሆናሉ:: የዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የምክክር መድረኩ ስያሜ፣ ዓላማ፣ ተግባርና ሃላፊነት፣ አመራር፣ አሰራርና የስነስርዓት ደንብ በፕሬዚዳንቶቹ ጉባኤ ሊወሰን ይችላል::

4/ የምክክር መድረኩ በፕሬዚዳንቶቹ ጉባኤ ውሳኔ የሚቋቋም ፅሕፈት ቤት ሊኖረው ይችላል::

5/ የምክክር መድረኩ ቃል አቀባይ በፕሬዚዳንቶች ጉባኤ ደንብ መሰረት በሰብሳቢነት የተመረጠው የመንግስት ዩኒቨርስቲ ፕሬዚዳንት ይሆናል::

6/ የምክክር መድረኩ ስራውን የሚያከናውነው በአባል ተቋማት አመታዊ የአባልነት መዋጮ፣ ስጦታዎችና ከሌሎች በሕግ ከተፈቀዱ ምንጮች በሚያገኘው ገንዘብ ይሆናል::

7/ የምክክር መድረኩ በአሰራሩ አግባብነት ያላቸው የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎችንም ማክበር ይኖርበታል::

8/ ሚኒስቴሩ እንዳስፈላጊነቱ በከፍተኛ ትምህርት ጉዳዮች ላይ ከምምክር መድረኩ ጋር ለመምከር ይችላል::

9/ በመንግስት ተቋማት የምክክር መድረክና አግባብነት ባለው ሌላ ሕግ መሰረት በተቋቋመ የግል ተቋማት ማህበር መካከል እንዳስፈላጊነቱ የምክክር ግንኙነት ሊኖር ይችላል::

10/ የመንግስት ተቋማት የምክክር መድረክ የዚህ ዓዋጅ ድንጋጌ ወይም የሌሎች ሕጎችን ድንጋጌዎች ተላልፎ ሲገኝ ግድፈቶቹን እስኪያስተካክል ድረስ በሚኒስቴሩ ትዕዛዝ ሊታገድ ይችላል::

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## ስለመንግሥት ተቋሞች መከፈል፣ መዋሃድ፣ የስም ለውጥና መዘጋት

### 59. የመንግሥት ተቋም መከፈል፣ መዋሃድ ወይም የስም ለውጥ

1/ አንድ የመንግስት ተቋም እንደአግባብነቱ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ወይም በሚመለከተው ክልል በሚወጣ ሕግ መሠረት ወደ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የመንግስት ተቋማት ሊከፈል ወይም ከሌላ የመንግስት ተቋም ጋር ሊዋሃድ ወይም ስሙ ሊለወጥ ይችላል::

2/ የመንግሥት ተቋማት መከፈል፣ መዋሃድ ወይም ስም መለወጥ የሚከናወነው የዚህ አዋጅና የሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጐች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ይሆናል::

### 60. የመንግሥት ተቋም መዘጋት

1/ እንደአግባብነቱ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ወይም በሚመለከተው የክልል አካል ውሳኔ የመንግሥት ተቋም እንዲዘጋ ማድረግ ይቻላል::

2/ የመንግሥት ተቋም መዘጋት በተገቢው ሚዲያ ይፋ መደረግ አለበት::

### 61. ስለመብትና ግዴታ መተላለፍ

1/ የመንግስት ተቋም በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ለሁለት ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ የመንግስት ተቋማት የተከፈለ ከሆነ መብቶቹና ግዴታዎቹ ለአዲሶቹ ተቋማት ይተላለፋሉ:: እያንዳንዱ አዲስ ተቋም ከነባሩ ተቋም የሚተላለፍለት መብትና ግዴታ መጠን መከፈሉ በተወሰነበት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ወይም የክልሉ ሕግ ይወሰናል::

2/ በዚህ አዋጅ መሠረት የተዋሃዱ ተቋማት መብትና ግዴታ ለአዲሱ ተቋም ይተላለፋሉ::

3/ በዚህ አዋጅ መሠረት የተከፈለው ወይም የተዋሃዱት የመንግስት ተቋማት ሕጋዊ ሰውነታቸውን አዲሶቹ ተቋማት በሕግ ከተቋቋሙበት ቀን ጀምሮ ያጣሉ::

4/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደ አግባብነቱ የስም ለውጥ ያደረገ ተቋምን በሚመለከትም ተፈፃሚ ይሆናሉ::

## ንዑስ ክፍል ሦስት

## ስለመንግሥት ተቋም በጀትና የገንዘብ አስተዳዳር

### 62. በጀት

1/ የፌዴራል መንግስት ወይም ክልሎች ለመንግስት ተቋማት በጀት የሚመድቡት በስትራቴጂክ ዕቅድ ስምምነት ላይ በተመሠረተ የጥቅል በጀት ሥርዓት መሠረት ይሆናል፡፡

2/ የመንግሥት ተቋም አስቀድሞ ስምምነት የተደረሰበትን የአምስት ዓመት ጠቋሚ ጥቅል በጀት ይመደብለታል፤ ሆኖም ጥቅል በጀቱ በየዓመቱ እየተገመገመ የሚስተካከል ይሆናል፡፡

3/ የመንግስት ተቋም የገንዘብ ፍላጐቱን ለማሟላት በዚህ አዋጅ አንቀፅ 66 እና 67 በተገለጸው መሠረትና በሕግ ከተፈቀዱ ሌሎች ምንጮች ገቢዎችን ማሰባሰብ ይችላል፡፡

4/ እያንዳንዱ የመንግስት ተቋም በተቋሙ ቦርድ የጸደቀውን የሥራ ዕቅድ፣ የስትራቴጂክ ዕቅድ ስምምነትን እንዲሁም የተቋሙን ዝግጁነት እየታየ ይህ አዋጅ ሥራ ላይ ከሚውልበት ቀን ጀምሮ ከአንድ ዓመት በኂላ በጥቅል በጀት ሥርዓት መሥራት ይጀምራል፡፡

5/ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (4) በተገለጸው ጊዜ ውስጥ የጥቅል በጀት አሠራር ተጠቃሚ ለመሆንና አስተዳደሩንም ባግባቡ ለመምራት ይችሉ ዘንድ የመንግስት ተቋማት የትምህርትና የገንዘብ መረጃዎችን የሚያስተዳድሩበትን አቅም መገንባት ይኖርባቸዋል፡፡

6/ የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የመንግስት ተቋማት የዚህን አንቀጽ ድንጋጌዎች ተግባራዊ ማድረግ እንዲችሉ ተገቢውን እገዛ ያደርጋል፡፡

7/ የመንግስት ተቋም ከሦስተኛ ወገኖች ሰጦታዎችን መቀበል ይችላል፤ ሆኖም የሚያገኘው ስጦታ በተቋሙ አቋም፣ ተልዕኮና ዓላማ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ የማይኖረው መሆን ይኖርበታል፡፡

8/ ማንኛውም የመንግስት ተቋም ከሦስተኛ ወገኖች ሰለሚያገኘው ገንዘብና ከኢንቨስትመንት ስለሚያገኘው ገቢ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴርና ለሚኒስቴሩ ወይም ለሚመለከተው የክልል አካል የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

## 63. <u>የድጎማ በጀት</u>

1/ በማንኛውም መንግሥታዊ ተቋም በአገልግሎት ላይ ያልዋለ የቀዳሚው ዓመት ጥቅል ባጀት የተቋሙ ድጎማ በጀት ሆኖ ወደሚቀጥለው የበጀት ዓመት እንዲተላለፍና ለተቋሙ አገልግሎት እንዲውል ሊደረግ ይችላል፡፡

2/ ተቋሙ የድጎማ በጀትን በካፒታል በጀት መልክ ብቻ ይጠቀምበታል፡፡

3/ የድጎማ በጀት ከዓመቱ ጥቅል በጀትና ከተቋሙ ገቢ ከሚገኘው ገንዘብ ጋር እንደተቋሙ አጠቃላይ ዓመታዊ በጀት በቦርዱ የሚጸድቅ ይሆናል፡፡

## 64. <u>የገንዘብ አስተዳደር</u>

1/ የመንግሥት ተቋም ኘሬዚዳንት የተቋሙን የገንዘብ ጉዳይ በሕግ፣ በቅልጥፍና፣ በውጤታማነት፣ በቁጠባና በግልፅነት መርሆዎች ላይ ተመሥርቶ የመምራትና የማስተዳደር ሃላፊነትና ተጠያቂነት ይኖርበታል፡፡

2/ ሕግ በሌላ ሁኔታ ያስቀመጣቸውን ሁኔታዎችና በጀትን አስቀድሞ በቦርድ የማፀደቅ አሰራር እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግሥት ተቋም በጸደቀለት የሥራ ዕቅድ መሠረት ገቢውን በነፃነት የመጠቀም መብት ይኖረዋል፡፡

3/ በጀት ባልፀደቀበት ወቅት ቦርዱ በጀቱን እስኪያፀድቀው ድረስ የመንግሥት ተቋም ፕሬዚዳንት የተቋሙ መደበኛ ስራ እንዳይስተጓጎል በቀዳሚው የበጀት ዘመን አሰራርና መጠን መሰረት ወጪ እንዲያደርግ በቦርዱ ሥልጣን ሊሰጠው ይችላል፡፡

## 65. የስትራተጂክ ዕቅድ ስምምነት

1/ የመንግሥት ተቋም ለአምስት ዓመት የሚቆይ የስትራተጂክ ዕቅድ ስምምነት እንዳግባብነቱ ከሚኒስቴሩ ወይም ከሚመለከተው የክልል አካል ጋር ያደርጋል፡፡

2/ የስትራተጂክ ዕቅዱ ስምምነት በተለይ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፤

ሀ) ስትራተጂክ ዓላማዎችን፣ የትኩረት አቅጣጫዎችን፣ የመማር-ማስተማር ውጤቶችንና ተቋማዊና የሰው ሃይል ልማትን፤

ለ) የታቀዱ የምርምር ኘሮጀክቶችንና ፕሮግራሞችን፤

ሐ) የትምህርት ፕሮግራሞችን እና በተከታታይና በርቀት የሚሰጡ ፕሮግራሞችን፤

መ) የተማሪዎችን ብዛትና የአካዳሚክ ሠራተኞችን ብዛትና የሙያ ብቃት ደረጃን፤

ሠ) የአካዳሚክ ሠራተኞቹን የብሔር ብሔረሰብ ተዋፅኦ ማመጣጠንን እና በከፍተኛ የኃላፊነት ቦታዎች የሴቶች ተሳትፎ ማሳደግን፣ ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች የሚደርገውን እገዛ ማጠናከርን የሚመለከቱ እርምጃዎችን፤

ረ) ከመንግሥት የሚጠበቀውን ጠቋሚ የጥቅል በጀትና ሊከሠት የሚችለውን የገንዘብ ክፍተት ከሌሎች ምንጮች ለማሟላት በተቋሙ የተገባውን ግዴታ፤

ሰ) ጠቋሚ ጥቅል በጀቱና ተቋሙ ራሱ አሟላለሁ ያለውን ገንዘብ ለእያንዳንዱ የስትራተጂክ ዕቅዱ ዘመን መመደቡን የሚያሳይ ጠቋሚ ክፍፍል፤

ሸ) የስትራተጂክ ዕቅዱ በጀት በቂ ሳይሆን ቢቀር የተቀመጠውን መፍትሄ፣

ቀ) ተገቢ የሒሳብ፣ የክትትል፣ የግምገማና ሪፖርትን የማቅረብ ሥርዓቶች መዘርጋታቸውን፡፡

3/ ስትራቴጂክ ዕቅዱ የተመሠረተባቸው ታሳቢዎች ከተለወጡ የስትራተጂክ ዕቅድ ስምምነቱ ሊሻሻል ይችላል፡፡

4/ የመንግሥት ተቋማት ቀጣዩን ረቂቅ የስትራተጂክ ዕቅድ ስምምነታቸውን በወቅቱ የስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመን ውስጥ እንዳግባብነቱ በሚኒስቴሩ ወይም በሚመለከተው የክልል አካል ያፀድቃሉ፡፡

## 66. ገቢን ስለማስገኘት

1/ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና አግባብነት ያላቸው ሌሎች ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም የመንግስት ተቋም በተቋሙ ፕሬዚዳንት ጥያቄና በቦርዱ ውሳኔ የገቢ ማስገኛ ድርጅትን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

2/ ድርጅቱ የራሱ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ሆኖ እንደማንኛውም የንግድ ድርጅት ሕጉ የሚጠይቀውን ሁሉ በማሟላት የሚሠራ ይሆናል፡፡

3/ ድርጅቱን ለማቋቋም የሚያስፈልገው የመነሻ ገንዘብ በመንግስት የሚመደብ በጀት ሊሆን ይችላል::

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ድርጅቱ የሚከተሉት የገቢ ምንጮች ሊኖሩት ይችላል፤

ሀ) ድርጅቱ ከሚሠጠው አገልግሎት ወይም ከሚያከናውነው ሥራ የሚገኝ ገቢ፤

ለ) የተቋሙ ሠራተኞች በፈቃደኝነት ከሚያደርጉት መዋጮ፤

ሐ) ለድርጅቱ ከሚሰጡ ሥጦታዎች፤

መ) ከሌሎች ሕጋዊ የገቢ ምንጮች::

5/ ተቋሙ የድርጅቱን የተጣራ ትርፍ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ለተልዕኮው መሣካት ሊጠቀምበት ይገባል::

6/ የድርጅቱ የፋይናንስ መግለጫዎች የበጀት ዓመቱ ካበቃበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወራት ውስጥ ለቦርዱ መቅረብ ይኖርባቸዋል::

## 67. <u>የገቢ ፈንድ</u>

1/ በመንግሥት ተቋም ውስጥ በቦርድ ተወስኖ እንደ አግባብነቱ በሚኒስቴሩ ወይም በሚመለከተው የክልል አካል ሲፀድቅ የገቢ ፈንድ ሊቋቋም ይችላል::

2/ የፈንዱ የገቢ ምንጮች የሚከተሉት ይሆናሉ፤

ሀ) በተቋሙ የገቢ ማስገኛ ድርጅት የሚደረግለት መዋጮ፤

ለ) በበጀት ዓመቱ ሥራ ላይ ያልዋለ የፈንዱ ገንዘብ፤

ሐ) ሥጦታዎች፤

መ) ሌሎች ሕጋዊ የገቢ ምንጮች::

3/ ፈንዱ ቦርዱ በሚያጸድቀው መሰረት ለተቋሙ ልዩ ልዩ የዓቅም ግንባታ ተግባራት፣ ለሽልማትና ሌሎች ተግባራት ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል::

4/ የፈንዱ አጠቃቀም የበጀት ስርዓትን የተከተለ ይሆናል::

## 68. <u>ሪፖርት ስለማቅረብና ስለቁጥጥር</u>

1/ ማንኛውም የመንግሥት ተቋም፣

ሀ) በስትራተጂክ ዕቅዱ ላይ የተመሠረተውንና ባግባቡ ተገምግሞ የፀደቀውን ዓመታዊ የአፈፃፀም ሪፖርትና በኦዲተር የተመረመረ የሂሳብ ሪፖርትን እንደአግባብነቱ ለሚኒስቴሩ ወይም ለሚመለከተው የክልል አካል ማቅረብና የበጀት ዓመቱ ትምህርታዊና ሌሎች መረጃዎችን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 27 በተደነገገው መሠረት ማሳተም፣

ለ) በማናቸውም ጊዜ በሚኒስቴሩ ወይም በሚመለከተው የክልል አካል የሚጠየቀውን መረጃ መስጠት፣

ይኖርበታል::

2/ ማንኛውም የመንግስት ተቋም እንደአግባብነቱ በሚኒስቴሩ ወይም በሚመለከተው የክልል አካል ሕግንና የስትራቴጂክ ዕቅድ ስምምነቱን ማክበሩን ለማረጋገጥ ቁጥጥር ሊደረግበት ይችላል::

3/ እንደአግባብነቱ ሚኒስቴሩ ወይም የሚመለከተው የክልል አካል ከሕግ፣ ከመንግስት ፖሊሲ፣ ከተቋሙ ተልዕኮ ወይም ደንቦች ጋር የሚጋጩ የቦርድ፣ የፕሬዚዳንት ወይም የሴኔት ውሳኔዎችን ሊሽር ይችላል፡፡

## 69. <u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1/ የመንግሥት ተቋም በፕሬዚዳንቱ ኃላፊነትና አስተዳደር ሥር የሚመራ የተቋሙ ግዴታዎችንም ታሳቢ ያደረገ የገቢና የወጪ ሒሳብን ጨምሮ አግባብነት ያለው የሂሳብ አያያዝና ሪፖርት የማቅረቢያ ሥርዓትን መዘርጋት ይኖርበታል፡፡

2/ የመንግስት ተቋም የደብል ኤንትሪ ሂሳብ አያያዝን የመከተል፣ ተቀጽላ የሆኑ ተግባራት ገቢና ወጪዎችን ከሌሎች ገቢዎችና ወጪዎች ለይቶ የመያዝ እና ለሁሉም የገቢና ወጪ ጉዳዮች የሒሳብ አያያዝ አጠቃላይ ሥርዓትን የመከተል ግዴታዎች ይኖሩበታል፡፡

3/ ሚኒስቴሩ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ጋር በመማከር የአንድ የመንግስት ተቋም ሀብትንና ዕዳን ለመለካት ቀለል ያለ የመመዘኛና የኦዲት ሥርዓት ለመጠቀም የሚያስችል የሂሳብ አያያዝና ሪፖርት አቀራረብ መመሪያ ማውጣት ይችላል፡፡

## 70. <u>ኦዲት</u>

1/ በማንኛውም የመንግሥት ተቋም ውስጥ ራሱን የቻለና ለፕሬዚዳንቱ ተጠሪ የሆነ የውስጥ ኦዲት ይቋቋማል፡፡

2/ የመንግሥት ተቋም የውስጥ ኦዲት ክፍል ኃላፊ በፕሬዚዳንቱ አቅራቢነት በቦርድ ይሾማል፡፡

3/ የውስጥ ኦዲት የተቋሙን ያፈፃፀም፣ የፋይናንስና ንብረት ኦዲት አከናውኖ ውጤቱን ለፕሬዚዳንቱና ለቦርዱ ያቀርባል፡፡

4/ እንደአግባብነቱ የፌዴራል ዋና ኦዲተር ወይም የክልሉ ዋና ኦዲተር ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የመንግሥት ተቋም ሂሳብ በቦርዱ በተሾመ የውጭ ኦዲተር በየአመቱ ተመርምሮ ውጤቱ ለፕሬዚዳንቱ፣ ለቦርዱና እንደአግባብነቱ ለሚኒስቴሩ ወይም ለሚመለከተው የክልል አካል መቅረብ ይኖርበታል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ስለግል ተቋማት</u>

## 71. <u>ተጠያቂነት</u>

1/ የግል ተቋም በሚቋቋምበት የመመሥረቻ ሰነድ እና በመተዳደሪያ ደንቡ በተደነገገው መሠረት አግባብነት ላለው አካል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ቢኖርም የግል ተቋም በትምህርት አሰጣጥና ምርምር ረገድ ስለሚያከናውናቸው ተግባራት ትክክለኛነት ተጠያቂነቱ ለሚኒስቴሩ ጭምር ይሆናል፡፡

## 72. <u>ስለግል ተቋማት ሃላፊነት</u>

1/ ማንኛውም የግል ተቋም የሚከተለው ኃላፊነት ይኖረዋል፤

ሀ) በሚኒስቴሩ የሚወጡ የተማሪዎች ቅበላን የሚመለከቱ መመሪያዎችን በጥብቅ የመከተል፤

ለ) ትምህርታዊ ይዘትን፣ የማስተማር ዘዴን፣ የተማሪዎች መመዘኛና የፈተናዎች ሥርአትን እና የውጤት ሥርአትን ጨምሮ ቢያንስ ለደረጃው የሚጠበቅበትን አነስተኛው የስርዓተ ትምህርት የጥራት ደረጃዎች የማረጋገጥ፤

ሐ) የአካዳሚክና የምርምር ክንውኖቹን አስመልክቶ ዓመታዊ ግለ-ግምገማና የተማሪዎችና የአካዳሚክ ሰራተኞች ግምገማ የማካሄድና ውጤቱን ለተቋሙ ማሕበረሰብ የማሳወቅና ለኤጀንሲውም ሪፖርት የማድረግ፤

መ) ከትምህርት ፕሮግራሞቹ መካከል በዲግሪ ለማስተማር ፈቃድ ባገኘባቸው የትምህርት መስኮች የሚከተለው ስርዓተ ትምህርትን፣ የቅበላ ዓቅምንና ትምህርቱን ለማጠናቀቅ የሚወስደውን መደበኛ ጊዜ በማካተት እውቅና የተሰጣቸው የትምህርት ፕሮግራሞችን ዝርዝር እና የአካዳሚክ ሰራተኞቹን ደረጃና የቅጥር ሁኔታቸውን የሚመለከቱ መረጃዎችን በቀላሉ ተደራሽ በሆነ መልኩ የመያዝና እነዚሁኑ አስመልክቶ ለተማሪዎቹና ለኅብረተሰቡ ትክክለኛ መረጃ የመስጠት፤

ሠ) በአመራርና በአስተዳደር አደረጃጀቱ፣ አሰራሩ፣ በአመራሩና በአስተዳደሩ ሃላፊዎች ብቃት፣ ተቋሙ የሚገኝበት አካባቢ፣ የትምህርት መገልገያዎችን ጨምሮ የካምፓሱ አጠቃላይ አካባቢያዊ ሁኔታ ተቋሙ ለተሰጠው ደረጃና ለሚያካሄዳቸው ስልጠናዎች፣ ላለው የተማሪዎችና የሰራተኞች ብዛትና ለተሰማራበት የትምህርት መስክ የሚመጥን መሆኑን የማረጋገጥ፤

ረ) የአምስት ዓመት ዝርዝር የትምህርት፣ የምርምርና የስልጠና እቅድን እንዲሁም በእቅዱ ላይ በየዓመቱ የተደረጉ ማስተካከያዎችን ለኤጀንሲው የማቅረብና እቅዱን ይፋ የማድረግ፤

ሰ) የትምህርት፣ የምርምርና የስልጠና ተግባራቱን በተመለከተ ዝርዝር አመታዊ የአፈፃፀም ሪፖርት በትምህርት ዓመቱ ማለቂያ ላይ ለኤጀንሲው ማቅረብና የትምህርት ግብአቶቹንና ውጤቶችን በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የማሳተም፤

ሸ) ሚኒስቴሩ የሚጠይቃቸውን መረጃዎች ያለ ምንም ክፍያ ሚኒስቴሩ በሚፈልግበት አይነትና በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የማቅረብ፤

ቀ) የመክሰር ውሳኔ እንዲሰጥበት ጥያቄ ከቀረበበት ይህንኑ ወዲያውኑ ለሚኒስቴሩ የማሳወቅ፤

በ) በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት ተግባሩን የማከናወን፡፡

2/ የግል ተቋም አመታዊ የአፈፃፀም ሪፖርት ከሌሎች ጉዳዮች በተጨማሪ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፤

ሀ) በአንድ የትምህርት ዘመን ውስጥ የተከናወኑ ተግባራትንና የተገኙ ውጤቶችን፤

ለ) የተቋሙን የሥራ አፈፃፀም ግምገማ ውጤት፤

ሐ) በትምህርት ዘመኑ በተቋሙ ውስጥ የተከሰቱ ሁኔታዎችን፤

መ) የትምህርቱን ዘመን ማብቃት ተከትሎ በተቋሙ የበላይ የአስተዳደር አካል የተፈረመበት ተቋሙ በከፍተኛ ትምህርት ተቋምነቱ ያለበትን አጠቃላይ ሁኔታ የሚያሳይ የግምገማ መግለጫ::

3/ ዓመታዊ የትግበራ ሪፖርት፣ የተቋሙ የረጅም ጊዜ ዕቅድ እና የትግበራው የግምገማ ውጤት ይፋ መደረግ ይኖርባቸዋል::

4/ ኤጀንሲው በዚህ አንቀፅ ሌሎች ድንጋጌዎችና በመደበኛ የአካዳሚክ ኦዲት አፈፃፀም ሳይገደብ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም የግል ተቋም ላይ ድንገተኛ የአካዳሚክ ኦዲት ወይም ማጣራት በማድረግ ተገቢ የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ ይችላል::

## 73. <u>የግል ተቋም የውስጥ ደንብ</u>

1/ የግል ተቋም የውስጥ ደንብ ስለተቋሙ የአስተዳደር አካላት፣ የተቋሙ የአስተዳደር አካላት ውሳኔ አሰጣጥ ሥነሥርአት፣ የአካዳሚክና ምርምር ጉዳዮች፣ የአካዳሚክ ማሕበረሰቡን መብትና ግዴታ እና ስለቅሬታ አፈታት ሥርአት መደንገግ ይኖርበታል::

2/ የግል ተቋም የውስጥ ደንብ የዚህን አዋጅ ወይም የማንኛውንም አግባብነት ያለው ሌላ ሕግ ድንጋጌዎች የማይቃረን መሆን ይኖርበታል::

3/ ኤጀንሲው የግል ተቋማት ስራ ላይ የዋለ ተገቢው የውስጥ ደንብ ያላቸው ስለመሆኑ ያረጋግጣል::

## 74. <u>የእውቅና ፈቃድ አስፈላጊ ስለመሆኑ</u>

1/ የግል ተቋምን ለማቋቋም፣ ደረጃውን ለማሳደግ ወይም ለመለወጥ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት ከኤጀንሲው እውቅናን ማግኘት ይኖርበታል::

2/ ማንኛውም የግል ተቋም ዲግሪ ለመስጠት የሚችለው እውቅና ባገኘበት የትምህርት ፕሮግራሞች፣ የትምህርት ዓይነትና በተፈቀደለት የተማሪዎች ብዛት ብቻ ይሆናል::

## 75. <u>የእውቅና ፈቃድ ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>

1/ የግል ተቋምን ለማቋቋም፣ ደረጃውን ለማሳደግ ወይም ለመለወጥ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው የእውቅና ፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻን ለኤጀንሲው ማቅረብ ይኖርበታል::

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቀርበው ማመልከቻ የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርበታል፤

ሀ) የተቋሙን ስምና ዋና አድራሻ፣

ለ) የተቋሙን የፋይናንስ አቅም፤

ሐ) ስለተቋሙ ተጠያቂ የሆነ አካልን ስምና አድራሻ፤

መ) የተቋሙን ባለቤቶች ስምና አድራሻ፤

ሠ) የተቋሙን ራዕይ፣ ተልእኮና ዓላማ፤

ረ) የትምህርት ፕሮግራሞችንና የትምህርት ደረጃዎችን፤

ሰ) ደረጃውን የጠበቀ ስርዓተ ትምህርት፣ የተቀጠሩና የሚቀጠሩበትን ጊዜ በመለየት በቅርቡ የሚቀጠሩ የአካዳሚክ ሠራተኞች በሙያ ዓይነትና በትምህርትና በማዕረግ ደረጃ እና የቴክኒክና የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ቁጥርና የትምህርት ደረጃ፤

ሸ) ተቋሙ ያለውና በቅርቡ የሚኖረው ለትምህርትና ለስልጠና የሚያስፈልጉ እንደ መፃህፍት፣ ቤተመፃሕፍት፣ ቤተሙከራ፣ የመማሪያ ክፍሎች፣ የትምህርትና የምርምር መገልገያዎች ዝርዝር፤

ቀ) የአዲስ ተማሪዎች ቅበላ መመዘኛ፤

በ) የተቋሙን ደረጃ፣ የአካዳሚክ ማሕበረሰቡን መብትና ግዴታ እና የቅሬታ ማስተናገጃ ሥርአትን የያዘ የውስጥ ደንብ፤

ተ) የተቋሙ አካዳሚያዊና አስተዳደራዊ ስራዎች የሚከናወኑበት የአመራርና የአስተዳደር ሥርአት፤

ቸ) የተቋሙን የአምስት አመት እቅድ፤

ኀ) አግባብነት ካላቸው የመንግስት አካላት የተሰጡ የኢንቨስትመንትና ሌሎች አስፈላጊ ፈቃዶችን::

3/ ኤጀንሲው የቀረበለትን ማመልከቻ መርምሮ፣

ሀ) በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የሰፈሩትን መመዘኛዎች ተቋሙ ማሟላቱን ሲያረጋግጥ የእውቅና ፈቃዱ ይሰጣል፤

ለ) ተቋሙ በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የሰፈሩትን መመዘኛዎች የማያሟላ ሆኖ ሲያገኘው የእውቅና ፈቃድ ጥያቄውን ውድቅ ያደርጋል::

4/ ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ተራ ፊደል (ለ) መሠረት የእውቅና ፈቃድ ጥያቄን ውድቅ ሲያደረግ ጥያቄው ተቀባይነት ያለገኘባቸውን ምክንያቶች ለአመልካቹ በፅሁፍ መግለፅ አለበት::

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ተራ ፊደል (ለ) መሠረት የእውቅና ፈቃድ የተከለከለ አመልካች የፈቃድ ክልከላው ከተገለፀበት ቀን አንስቶ በ90 ቀናት ውስጥ አስፈላጊ የሆኑትን መመዘኛዎች በማሟላት እንደገና ለማመልከት ይችላል፤ ሆኖም የእውቅና ፈቃድ በድጋሚ የተከለከለ አመልካች ዳግም ከተከለከለበት ጊዜ ጀምሮ ከአንድ ዓመት በኋላ ሊያመለክት ይችላል::

6/ ኤጀንሲው የእውቅና ፈቃድ ክልከላ ውሳኔውን እንደ ክልከላው ሁኔታ በተገቢ ሚዲያ ለህዝብ መግለጽ ይኖርበታል::

**76. <u>የእውቅና ፈቃድ ስለመስጠት</u>**

1/ ኤጀንሲው የቀረበለትን የእውቅና ፈቃድ ማመልከቻ መርምሮ በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተመለከቱት መመዘኛዎችን ተቋሙ ማሟላቱን አረጋግጦ በተገቢ ጊዜ ውስጥ የእውቅና ፈቃዱን ይሰጣል::

2/ በኤጀንሲው የሚሰጠው የእውቀና ፈቃድ፣

ሀ) የተቋሙን ስምና አድራሻን፣

ለ) የተቋሙን ደረጃ፣ ፕሮግራሞችና ስርዓተ ትምህርትን፣

መ) የመምህራኑ ብዛትና የትምህርት ደረጃ ስብጥርን፣

ሠ) የ ተማሪዎች ብዛትና ትምህርቱ የሚሰጥበት ቦታን፣

ረ) የእውቅና ፈቃዱ የተሰጠበትን ቀንና የሚያገለግልበትን የጊዜ ገደብን፣

ሰ) የእውቅና ፈቃዱን የሰጠውን ሃላፊ ስምና ፊርማ እና የኤጀንሲው ማህተም፣

መያዝ ይኖርበታል።

3/ ኤጀንሲው የእውቅና ፈቃድ መሰጠቱን አስመልክቶ በተገቢ ሚዲያ ለህዝብ መግለጽ ይኖርበታል።

## 77. የእውቅና ፈቃድ ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ

1/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 76 መሠረት ለግል ተቋም የተሰጠ የመጀመሪያው የእውቅና ፈቃድ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለ3 ዓመታት ያገለግላል።

2/ ለግል ተቋም የተሰጠ የእውቅና ፈቃድ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ እንዳበቃና በቀጣይም በየአምስት ዓመቱ አዲስ የትምህርት ዘመን ከመጀመሩ በፊት መታደስ ይኖርበታል።

## 78. የእውቅና ፈቃድን ለማሳደስ ስለሚቀርብ ማመልከቻ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 77 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የእውቅና ፈቃድ እንዲታደስ የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፤

1/ የእውቅና ፈቃድ እንዲሰጥ ወይም ቀደም ሲል እንዲታደስ ሲጠየቅ ለኤጀንሲው ከቀረበው ማመልከቻ ጋር ቀርበው የነበሩትን መረጃዎችና የትምህርት ግብአቶችና መገልገያዎች አሁን ያሉበትን ደረጃ የሚገልፅ ሪፖርትን፤

2/ በተቋሙ የጥራት ማጎልበት ስርዓት የተካሄደ የግለ-ግምገማ ውጤት ሪፖርትን፤

3/ የተቋሙ የአካዳሚክ፣ የቴክኒክና የድጋፍ ሰጪ ቋሚ ሠራተኞች ዝርዝርን፤

4/ በየዓመቱ ተቋሙ በሚሰጠው በእያንዳንዱ የትምህርት መስክ የተመዘገቡ ተማሪዎች ዝርዝርን፤

5/ ለትምህርትና ለምርምር እንዲሁም ከትምህርት ጋር ተዛማጅነት ላላቸው ሌሎች ተግባራት ማከናወኛ የተዘጋጁ መግልገያዎችንና የትምህርት መረጃዎች ዝርዝርን፤

6/ በኦዲተር የተመረመሩ የመጨረሻዎቹን ሦስት ዓመታት የተቋሙ የሂሳብ ሪፖርቶችን፤

7/ ሚኒስቴሩ ባወጣው መመሪያ መሠረት በኤጀንሲው የሚጠየቁ ሌሎች መረጃዎችን።

## 79. የእውቅና ፈቃድ ለማደስ ስለሚቀርብ ማመልከቻ ውሳኔ አሰጣጥ

1/ ኤጀንሲው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 78 መሠረት የእውቅና ፈቃድ እድሳት ጥያቄ ሲቀርብለት በገምጋሚ ኮሚቴው አማካይነት፤

ሀ) በተቋሙ የቀረበውን ግለ-ግምገማ ሰነድና ሌሎች ሪፖርቶችን ይመረምራል፣ በነዚሁ ውስጥ የተካተቱ መረጃዎችንና ስታትስቲካዊ መግለጫዎችን ትክክለኛነት ያረጋግጣል፤

ለ) በተቋሙ የሚሰጡ ፕሮግራሞችን ባገናዘበ መልክ፣

(1) የተቋሙን አካዳሚያዊና አስተዳደራዊ መሠረተ ልማቶች፣

(2) ሥርአተ ትምህርትን፣ የመማር ማስተማር ጥራትን፣ የተማሪዎች መረጃዎችን፣ የትምህርት መገልገያዎችን፣ ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎና የመምህራኑ ብቃትን ጨምሮ የተማሪዎች የትምህርቱ ጥራት ግምገማን፣

(3) የድጋፊ ሰጪ ሰራተኞች ዝርዝርና የትምህርት ደረጃን፣

(4) የምርምር ስራዎቹን መጠንና አግባብነት፣

በጥልቀት ይገመግማል፤

2/ ኤጀንሲው በገምጋሚ ኮሚቴው ሪፖርት መሠረት፣

ሀ) በዚህን አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የሰፈሩትን መመዘኛዎች በተቋሙ መሟላታቸውን ካረጋገጠ የእውቅና ፈቃዱ እንዲታደስለት ያደርጋል፤ ወይም

ለ) በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የሰፈሩትን መመዘኛዎች በተቋሙ አለመሟላታቸውን ካረጋገጠ የእውቅና ፈቃድ እድሳት ጥያቄውን ውድቅ ያደርጋል።

3/ ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ተራ ፊደል (ለ) መሠረት የእውቅና ፈቃድ እድሳት ጥያቄ ውድቅ እንዲሆን ከወሰነ ተቋሙ ያለበትን ደረጃ መሆን ከሚገባው ደረጃ ጋር በማነፃፀር ከሚያሳይ ዝርዝር መግለጫ ጋር በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ሊወሰዱ ስለሚገባቸው የማስተካከያ እርምጃዎች አመልካቹን በጽሑፍ ያሳውቀዋል።

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ተራ ፊደል (ለ) መሠረት የእውቅና ፈቃድ እድሳት የተከለከለ ተቋም በኤጀንሲው የተገለጹትን የማስተካከያ እርምጃዎች በተወሰነለት የጊዜ ገደብ ውስጥ በመውሰድ ተፈላጊ መመዘኛዎችን አሟልቶ እንደገና ማመልከት ይችላል።

5/ ኤጀንሲው የእውቅና ፈቃድ እድሳት ጥያቄን ውድቅ ያደረገበትን የመጨረሻ ውሳኔ በተገቢው ሚዲያ ለህዝብ መግለጽ ይኖርበታል።

6/ የእውቅና ፈቃድ እድሳት የተከለከለ ተቋም የተቀበላቸውን ተማሪዎችና ሰልጣኞች ቢኖሩ አግባብ ባላቸው ሌሎች ተቋማት ተዛውረው ትምህርታቸውን እንዲያጠናቅቁ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል።

## 80. <u>የእውቅና ፈቃድ እድሳት</u>

1/ የታደሰው እውቅና ፈቃድ፣

ሀ) የተቋሙን ስምና አድራሻን፣

ለ) የተቋሙን ደረጃ፣ ፕሮግራሞችና ስርዓተ ትምህርትን፣

መ) የ መምህራኑ ብዛትና የትምህርት ደረጃ ስብጥርን፣

ሠ) የ ተማሪዎች ብዛትና ትምህርቱ የሚሰጥበት ቦታን፣

ረ) የእውቅና ፈቃዱ የታደሰበት ቀንና የሚያገለግልበት የጊዜ ገደብን፣

ሰ) የእውቅና ፈቃዱን ያደሰውን ሃላፊ ስምና ፊርማ እና የኤጀንሲውን ማህተም፣

መያዝ አለበት::

2/ ኤጀንሲው የእውቅና ፈቃድ መታደሱን አስመልክቶ በተገቢ ሚዲያ ለህዝብ መግለጽ ይኖርበታል::

## 81. <u>የእውቅና ፈቃድን ስለመሰረዝ</u>

1/ ኤጀንሲው ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ የግል ተቋም የእውቅና ፈቃድን ሊሰርዝ ይችላል፤

ሀ) የእውቅና ፈቃዱ የተሰጠው በሀሰተኛ ማስረጃ ላይ ተመሥርቶ መሆኑን ሲረጋገጥ፤

ለ) ተቋሙ የሚፈለግበትን ደረጃ ባለመጠበቁ ወይም የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም የሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሕጐች ወይም ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን ጥሶ በመገኘቱ በኤጀንሲው ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት በማስጠንቀቂያው በተገለፀው የጊዜ ገደብ ጉድለቶችን ሳያስተካክል ሲቀር፤

ሐ) ተቋሙ ሲፈርስ ወይም ሥራውን ሲያቆም::

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ተራ ፊደል (ሀ) ወይም ተራ ፊደል (ለ) መሠረት የሚወሰነው የእውቅና ፈቃድ ስረዛ አዲስ የትምህርት ዘመን ከመጀመሩ በፊት ተፈጻሚ ይሆናል::

3/ የዕውቅና ፈቃዱ የተሠረዘ የግል ተቋም ተማሪዎቹና ሰልጣኞቹ ትምህርታቸውን አግባብነት ባላቸው ሌሎች ተቋማት እንዲፈፅሙ ማድረግ ይኖርበታል::

## 82. <u>አቤቱታ ስለማቅረብ</u>

1/ በኤጀንሲው ውሳኔ የእውቅና ፈቃድ እንዲሰጠው ወይም የእውቅና ፈቃድ እንዲታደስለት ያቀረበው ማመልከቻን ውድቅ የተደረገበት ወይም የዕውቅና ፈቃዱ የተሠረዘበት ማንኛውም ተቋም ውሳኔው በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔው እንደገና እንዲታይለት ለሚኒስቴሩ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል::

2/ ሚኒስቴሩ አቤቱታውን መርምሮ የውሳኔ ሃሳብ የሚያቀርብ የይግባኝ መርማሪ ኮሚቴ ያቋቁማል::

3/ ሚኒስቴሩ በቀረበው ማመልከቻ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት አመልካቹ ቀርቦ እንዲሰማ ማድረግ ይኖርበታል::

## 83. <u>ምትክ የእውቅና ፈቃድ ስለመስጠት</u>

1/ የእውቅና ፈቃድ የተበላሸበት ወይም የጠፋበት ማንኛውም የግል ተቋም ምትክ ፈቃድ እንዲሰጠው ለኤጀንሲው ለማመልከት ይችላል፡፡

2/ ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ጥያቄ ሲቀርብለት፣

ሀ) አመልካቹ የተበላሸውን የዕውቅና ፈቃድ እንዲመልስ፣

ለ) የዕውቅና ፈቃዱ የጠፋ ከሆነ ስለመጥፋቱ ሕጋዊ ማረጋገጫ እንዲያቀርብ፣

ካደረገ በኋላ ምትክ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

**84. <u>የእውቅና ፈቃድ ስለመመለስ</u>**

1/ በዚህ አዋጅ መሠረት የእውቅና ፈቃድ የተሰረዘበት ተቋም ፈቃዱ በተሰረዘ በ15 ቀናት ውስጥ ፈቃዱን ለኤጀንሲው መመለስ አለበት፡፡

2/ አንድ ተቋም ደረጃውን የለወጠ፣ ከሌላ ጋር የተዋሃደ፣ የተከፈለ ወይም ስሙን የለወጠ ከሆነ በዚሁ መሠረት ተገቢውን አዲስ የእውቅና ፈቃድ እንዲሰጠው የቀድሞውን ፈቃድ ለኤጀንሲው መመለስ ይኖርበታል፡፡

**85. <u>ስለ እውቅና ፈቃድ ክፍያ</u>**

የእውቅና ፈቃድ ክፍያ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

**86. <u>ስለ የመንግሥት ድጎማ</u>**

1/ መንግስት ብቁ የሰው ሃይልን በማፍራት የአገሪቱ የልማት ፍላጎት የሚጠይቀው የማስፈፀም ዓቅም ግንባታን ለማጠናከር የሚሰሩ ለትርፍ ያልተቋቋሙ የግል ተቋማትን ለማበረታታት የባጀት ድጎማ ወይም የዓቅም ግንባታ ድጋፍ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2/ ሚኒስቴሩ ለትርፍ ያልተቋቋሙ የግል ተቋማት፣

ሀ) በቅደመ-ምረቃና ድህረ-ምረቃ ፕሮግራሞች በተቋማቱ ውስጥ ተመዝግበው የሚማሩትን መደበኛ ተማሪዎችና ከእነርሱም መካከል በነፃ የሚማሩትን ተማሪዎች ብዛት፣

ለ) ተቋማቱ የቋሚ ቅጥር ዕድል ያስገኙላቸውን የአካዳሚክ ሠራተኞች ብዛት፣

ሐ) የተቋማቱን የትምህርት ጥራት፣

መ) ተቋማቱ በትምህርትና ምርምር ረገድ ያስመዘገቧቸውን ውጤቶች፣ እና

ሠ) ተቋማቱ ራሳቸው አገልግሎቶቻቸውን ለማስፋፋት ያፈሰሱትን ሀብት፣

በማገናዘብ ከመንግስት የበጀት ድጎማ ወይም የዓቅም ግንባታ ድጋፍ እንዲሰጣቸው ሊያመለክቱ ስለሚችሉበትና አጠቃቀሙን ስለሚከታተልበት ሥርዓት መመሪያ ያወጣል፡፡

3/ ለትርፍ ያልተቋቋሙ የግል ተቋማት፣

ሀ) በተወሰነ መስክ ወይም ተወራራሽ በሆኑ መስኮች ለሚሰጧቸው የዲግሪ ፕሮግራሞችና ጥናቶች ድጋፍ እንዲሆን፣ ወይም

ለ) የሚያካሂዷቸው የዲግሪ ፕሮግራሞች የላቀ ጥራት ያሏቸው ስለመሆናቸው በኤጀንሲው ተረጋግጦ እንዲበረታቱ ለማድረግ፣

አስቀድሞ ለዚሁ ዓላማ ከተያዘው የመንግስት ገንዘብ ላይ ተጨማሪ ድጎማ ሊደረግላቸው ይችላል፡፡

**87. የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት**

የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች እንደአግባብነቱ ለመንግሥት ተቋማት ስለሚሰጥ የዕውቅና ፈቃድም ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## ክፍል አምስት

## ስለአስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር

**88. የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር**

ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች የተሰጠውን ሃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፤

1/ የከፍተኛ ትምህርት ሥርአተ ትምህርት ዝግጅትና አተገባበር ከአለም አቀፍ እድገት እና ከአገራዊ ፍላጐትና መመዘኛዎች ጋር የሚመጣጠን መሆኑን ያረጋግጣል፤

2/ በባችለር፣ በማስትሬት፣ በህክምና ስፔሻሊቲ እና በዶክትሬት ፕሮግራሞች ትምህርት ለመስጠት የሚያስችሉ መሰረታዊ የብቃት መመዘኛዎችን ይወስናል፤

3/ የመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ፖሊሲና ስትራቴጂ ተግባራዊ መደረጉን ያረጋግጣል፤

4/ በዚህ አዋጅ፣ በመንግስት ፖሊሲና እንዳስፈላጊነቱ በየጊዜው በሚያወጣቸው መሥፈርቶች መሠረት በመንግስታዊ ተቋማት ደረጃና በመንግስታዊ ተቋማት ውስጥ የሚደረጉት የተማሪዎች ምደባ እና የተማሪዎች ቅበላ ስርዓቱ ባጠቃላይ ፍትሃዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

5/ ሃገራዊ አነስተኛ የትምህርት ብቃት መመዘኛዎችን፣ የሙያ ስነምግባር ደንቦችን እና ተቋማት ሊከተሏቸው የሚገቡ የአሰራር ሥነሥርአትን ያወጣል፤

6/ መንግስት ለመንግስት ተቋማት ጥቅል በጀት የሚመድብበትን መሥፈርትና ሥርአት ይወስናል፤

7/ በተቋማት መካከል ትብብርና የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

8/ ለተቋማት የውስጥ የጥራት ማጎልበቻ ሥርአት ድጋፍ ይሰጣል፤

9/ የመንግስት ተቋም ስትራቴጂክ እቅድን ያፀድቃል፣ በሥራ ላይ መዋሉንም ያረጋግጣል፤

10/ የአገሪቱ የከፍተኛ ባለሙያ የሰው ሃይል ፍላጐትን ለመለየትና ይህንኑ ለማሟላት ጥናት ያካሂዳል፤

11/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በከፍተኛ ትምህርት መስክ የሚደረግ ኢንቨስትመንትን ያበረታታል፤

12/ የመንግስት አካላት፣ የሙያ ማሕበራት፣ የንግድ ማሕበራት እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሰዎች በትምህርት፣ በስልጠና፣ በተግባር ልምምድ፣ በምርምር እና በቴክኖሎጂ ሽግግር ጉዳዮች ላይ ከተቋማት ጋር በጋራ ወይም በትብብር እንዲሰሩ ያበረታታል።

13/ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ተግባራዊነት ያረጋግጣል።

## 89. የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር

ኤጀንሲው በዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች የተሰጠው ሃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፤

1/ በግልጽ የሠፈሩ የግምገማና የእውቅና አሰጣጥ መመዘኛዎችንና ሥርአትን በማዘጋጀት በስራ ላይ ያውላል፤

2/ በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ተቋምን ወይም የተቋምን ክፍሎች ለመክፈት ወይም ለማሻሻል የሚቀርብ ፕሮጀክትን በመገምገም ለሚኒስቴሩ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤

3/ የእውቅና ፈቃድ ወይም እድሳት ለመስጠት የሚያስችል የተቋም ብቃትና የትምህርትና የስልጠና አግባብነትና ጥራት ግምገማን ያካሂዳል፤

4/ የተቋም የትምህርት አግባብነትና ጥራት ማጎልበቻ ስርዓት የከፍተኛ ትምህርት ጥራትን ማረጋገጥ ስለመቻሉ ግምገማ ያካሂዳል፤

5/ በማንኛውም ተቋም የሚሰጡ የከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ከአገሪቱ የኢኮኖሚና የማሕበራዊ ፍላጎትና አግባብነት ካላቸው ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ጋር መገናዘባቸውን ያረጋግጣል፤

6/ የግምገማ ኮሚቴዎችን ያደራጃል፤ ሃላፊነታቸውና አሰራራቸውን ይወስናል፤ ስራቸውን ሲያከናውኑ የሚከተሉትን የስነ ምግባር መመሪያም ያወጣል፤

7/ በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ለእውቅና ፈቃድና ለእውቅና ፈቃድ እድሳት የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን ይመረምራል፤ይወስናል፤

8/ የትምህርት አግባብነትና ጥራትን ለመገምገም ወይም የእውቅና ፈቃድ ወይም የእውቅና ፈቃድ እድሳት ጥያቄዎችን ለመርመር አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ አግባብነት ካላቸው አካላት መረጃና አስተያየት ይጠይቃል፤

9/ በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተቀመጡትን የትምህርት አግባብነትና ጥራት ደረጃዎች መከተላቸውን ለማረጋገጥ ተቋማትን በመገምገም የሚደረሰባቸውን የግምገማ ግኝቶች ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤

10/ የተቋማትን ደረጃ ለመወሰን የሚያስችሉ መመዘኛዎችንና መመሪያዎችን በማዘጋጀት ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤

11/ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የተቋማትን መዋሃድ፣ መከፈል፣ መዘጋት ወይም የስም ለውጥ አስመልክቶ ለሚኒስቴሩ ምክር ይሰጣል፤

12/ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ በውጭ አገር የተቋቋሙ ተቋማት ወይም የነሱ ቅርንጫፎች በተቋቋሙባቸው አገሮች እውቅና ያገኙ መሆናቸውንና በዚህ አዋጅና

ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተቀመጡ የትምህርት አግባብነትና ጥራት ደረጃዎችን ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፤

13/ በውጭ ተቋማት የሚሰጡ የትምህርት ፕሮግራሞችና የነዚህኑ ተቋማት ደረጃና አቋም የሚመለከቱ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያሰራጫል፤

14/ የከፍተኛ ትምህርት ማስረጃዎች የአቻነት መወሰኛ ሥርአት ያዘጋጃል፣ በውጭ አገር ተቋማት የተሰጡ የትምህርት ማስረጃዎችን የአቻ ግምት ይሰጣል፤

15/ እውቅና ያገኙ ተቋማትንና ደረጃቸውን፣ ዋና ዋና ክፍሎቻቸውንና የትኩረት መስኮቻቸውን የሚመለከቱ ወቅታዊ መረጃዎችን ይይዛል፣ አግባብነት ባላቸው የመገናኛ ዘዴዎች መረጃዎቹን በየጊዜው ለሕዝብ ያሰራጫል::

## 90. የማዕከሉ ሥልጣንና ተግባር

በዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች የተሰጠው ሃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ማዕከሉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፤

1/ የከፍተኛ ትምህርትንና የተቋማትን እድገት አስመልክቶ አገር አቀፍ ስትራቴጂ ያዘጋጃል፤

2/ በከፍተኛ ትምህርት ሥርአት ውስጥ ትምህርትና ምርምር ስለሚያድጉበት ሁኔታ የረጅም ጊዜ አገር አቀፍ እቅድ ያዘጋጃል፤

3/ የተቋማትን የትምህርትና ምርምር ጥራትን፣ የአካዳሚክ ሰራተኞችን ብቃት እንዲሁም የትምህርት ፕሮግራሞችን ለማሳደግ የሚያግዙ አገር አቀፍ የመነሻ ሃሳቦችን ያቀርባል፤

4/ በተቋም ደረጃ የሚወጣ እቅድና ስትራቴጂ በአገር አቀፍ ደረጃ ከሚወጣ አጠቃላይ የከፍተኛ ትምህርት እቅድና ስትራቴጂ ጋር የተጣጣመ መሆኑን ያረጋግጣል፤ ለዚህም ከተቋማት ጋር በቅርበት ይሠራል፤ የስትራቴጂክ እቅድ ስምምነትን ይመረምራል፤ ሲፀድቅም አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

5/ ለእያንዳንዱ የመንግስት ተቋም ስለሚሰጥ የጥቅል በጀት ምደባ ሃሳብን ያመነጫል፤ የጥቅል በጀት ምደባ አፈፃፀምን ይከታተላል፤

6/ የተቋማትን ዓመታዊ የትምህርት፣ የምርምር፣ የፋይናንስና ሌሎች ስታትስቲካዊ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ይተነትናል፤ እንደተገቢነቱም አትሞ ለሚመለከታቸው ያሰራጫል፤

7/ ተቋማት የተለያየ መጠን ባለው የልማት በጀት መልክ የማበረታቻ ሽልማት ስለሚያገኙበት መመዘኛና አሰራር ለሚኒስቴሩ ሃሳብ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም በስራ ላይ ያውላል፤

8/ የከፍተኛ ትምህርት ከአገሪቱ አጠቃላይ የማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ፍላጎት ጋር የተጣጣመ መሆኑንና በአካሄዱ ከአለም አቀፉ እውነታ ጋር እኩል የሚራመድ መሆኑን ያረጋግጣል፤

9/ ቀልጣፋ የከፍተኛ ትምህርት አስተዳደር፣ አመራርና ማኔጅመንት እንዲኖር ለማድረግ ስለሚቻልበት ሁኔታ ሚኒስቴሩን ያማክራል፤

10/ በወቅታዊ የፖሊሲ ጉዳዮች፣ አሰራርና ውጤቶች ላይ ምርምርና ጥናት በማድረግ ትክክለኛ የአሠራር አቅጣጫዎችን ይጠቁማል፤ ለማሻሻያ፣ ለለውጥና ለልማት የእውቀት ግብአት ምንጭ ሆኖ ያገለግላል፤

11/ በአገሪቱ የከፍተኛ ትምህርት ማሻሻያና ልማት ስትራቴጂና እቅድ ላይ ሃሳብ ይሰጣል፤

12/ በሃላፊነቱ ማዕከልነት በአገራዊ ተቋማት መካከል ትብብርን ያጎለብታል፤ የከፍተኛ ትምህርት ጉዳዮችን ከሚያከናውኑ ተመሳሳይ የውጭ አገር አካላት ጋር ግንኙነት ይመሰርታል፤

13) በማቋቋሚያ ሕጉ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## ክፍል ስድስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 91. የአገልግሎት ክፍያዎች

1/ የዚህ አዋጅ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ የመንግስት ተቋም ለሚሰጣቸው የትምህርት እና ሌሎች አገልግሎቶች ክፍያ መጠየቅ ይችላል፤የክፊያው ዓይነት፣ መጠንና የክፊያው አፈጻጸም ስርዓት ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

2/ የግል ተቋም ክፍያ የሚያስከፍልበት የውስጥ ደንብ የሚወሰነው በተቋሙ የመመስረቻ ሰነድ ውስጥ ሥልጣን በተሠጠው አካል ይሆናል።

### 92. ወጪ ስለመጋራት

1/ የማንኛውም በመንግሥት ተቋም ተማሪ የሆነና ለትምህርቱ አስቀድሞ የማይከፍል ኢትዮጵያዊ የትምህርቱን ወጪ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ስለወጪ መጋራት በሚያወጣው ደንብ መሰረት በገንዘብ ወይም በአገልግሎት እንዲሸፍን ይደረጋል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት ሥርዓት እና ሥርዓቱ በየጊዜው የሚከለስበት ሁኔታ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ መሠረት ይፈጸማል።

### 93. አገልግሎት በሌሎች ወገኖች እንዲሰጥ ስለማድረግ

1/ ማንኛውም የመንግሥት ተቋም ተገቢና ተግባራዊ ሊደረግ የሚችል ሆኖ ሲያገኘው የድጋፍ ሰጪ አገልግሎቶችን በሌሎች አገልግሎት አቅራቢዎች እንዲሰጥ ሊያደረግ ይችላል።

2/ ማንኛውም የመንግሥት ተቋም አገልግሎት በሌሎች አቅራቢዎች እንዲሰጥ ሲያደረግ የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ለዋጋው ተመጣጣኝ የሆነ አገልግሎት ለማግኘት መቻላቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል።

### 94. የመሬት አቅርቦት

መንግስት አግባብነት ባላቸው ሕጐችና ፖሊሲዎች መሠረት ተቋማት ለትምህርት፣ ለምርምርና ሕብረተሰብ አገልግሎት ተግባራት ማከናወኛ የሚያስፈልጋቸውን መሬት ሊሰጥ ይችላል::

**95.** ኃላፊነት

1/ ማንኛውም ሰው የዚህ አዋጅ ወይም ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች ድንጋጌዎችን ተላልፎ ከተገኘ በሕግ መሠረት የፍትሐ ብሔርና የወንጀል ሃላፊነት ይኖርበታል::

2/ እውቅና ያለው የትምህርት ማስረጃ ሳይሰጠው እንደተሰጠው አስመስሎ ያቀረበ ማንኛውም ሰው ወይም ዕውቅና ላልተሰጠው የትምህርት ፕሮግራም ማስረጃ የሰጠ ወይም የሃሰት የትምህርት ማስረጃ የሰጠ ማንኛውም ሰው በሕግ መሠረት የፍትሐ ብሔርና የወንጀል ኃላፊነት ይኖርበታል::

**96.** የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1/ በአዋጅ ቁጥር 351/1995 መሠረት የተሰጡ የቅድመ እውቅናና የእውቅና ፈቃዶች በዚህ አዋጅ መሠረት እንደተሰጡ ተደርገው ይቆጠራሉ::

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም፣ የግል ተቋማት ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን አንስቶ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን መሥፈርቶች ሙሉ በሙሉ ለማሟላት የማስተካከያ እርምጃዎች መውሰድ አለባቸው::

3/ ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት መታየት የጀመሩና ያላለቁ ጉዳዮች በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ይወሰናሉ::

**97.** ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል::

2/ ሚኒስቴሩ ይህንን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል::

**98.** የተሻሩ ሕጐች

1/ የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 351/1995 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፤ ሆኖም በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችና መመሪዎች ድንጋጌዎች ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር የሚጣጣሙ እስከሆነ ድረስ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች እስከሚተኩ ድረስ ተፈጻሚነታቸው ይቀጥላል::

2/ ከዚህ አዋጅ ጋር የማይጣጣሙ ሕጐች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች ወይም የአሰራር ልምዶች በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም::

**99.** አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

*ይህ አዋጅ ከ ---------------- ቀን 2001 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡*

*አዲስ አበባ ----------- ቀን ------------- 2001 ዓ.ም*

*ግርማ ወልደጊዮርጊስ*
*የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ*
*ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት*